# የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ሚና በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በብቸና ከተማ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት


በገብረመድህን ተስፋው

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

ነሀሴ

2011 ዓ.ም

# በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በብቸና ከተማ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማክቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ሚና መመርመር

የትምህርት ማስተርስ ድግሪ በአማርኛ

(ማሟያ ጥናት)


በገብረመድህን ተስፋው

አማካሪ፡ -

ጥበቡ ሽቴ (PhD)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር


ነሀሴ 2011 ዓ.ም

ጅማ

## ማረጋገጫ

የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ፋይዳ መመርመር በሚል ርዕስ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በገብረመድህን ተስፋው በአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት በውጪ በውስጥ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

### የፈታኞች ቦርድ

አማካሪ

ስም ____________________________ ፊርማ_________________ ቀን________________

_

የውጪ ፈታኝ ስም_______________________ ፊርማ_________________ ቀን_________________

የውስጥ ፈታኝ ስም______________________ ፊርማ_________________ ቀን_________________

## ምስጋና


በመጀመሪያ ሁሉ ነገር በጊዜው እንዲፈፀም ለሚያደርግ ለልዑል እግዚአብሔር ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ሚሪያም ጋር ምስጋና ይገባዋል!!

ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንዴት መስራት እንዳለብኝ አቅጣጫ በማሳየት፣ የጥናቱን ረቂቅ በሚያምኛ ገንቢ አስተያየት በመስጠት አሁን ያለውን ቅርፅ እንዲይዝና በወቅቱ እንዲከናወን በማበረታታት ለፍፃሜ እንዲደርስ እገዛ ሲያደርጉልኝ ለነበሩት አማካሪዬ ለዶክተር ጥበቡ ሽቴ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

እንዲሁም ጥናቴን ጀምሬ እስከ ማጠናቀቅ ድረስ ሀሳብ በማካፈል፣ ፈተና በሚፈተንና በሚያም አስፈላጊ ድጋፎችን በማድረግ ላልተለዩኝ የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

ይህን ጥናት እና ምርምር የተሳካ እንዲሆን የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ትምህርቴን ጀምሬ እስካጠናቅቅ ድረስ በሀሳብም ሆነ በቁሳቁስ ድጋፍ በመስጠት ከጎኔ ላልተለዩኝ ቤተሰቦቼ እና ጓደኞቼ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

## ይዘት ማውጫ

**ርዕስ**

**ገጽ**

ምስጋና ..... i

ይዘት ማውጫ..... ii

የሠንጠረዥ ማውጫ..... iv

አጠቃሎ..... iv

ምዕራፍ አንድ..... 1

መግቢያ ..... 1

1.1.የጥናቱ ዳራ..... 1

1.2. የጥናቱ ማሻሻችግር ..... 5

1.3. የጥናቱ ዓላማ..... 8

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 8

1.5. የጥናቱ ወሰን ..... 8

1.6. የጥናቱ ውስንነት..... 9

1.7. የምርምሩ ቁልፍ ቃላትብያኔ ..... 9

ምዕራፍ ሁለት..... 10

ክለሳ ድርሳናት..... 10

2.1. የማንበብ ምንነት..... 10

2.2. የአንብቦ መረዳት ምንነት ..... 11

2.3. አንብቦ መረዳትን የማስተማር ሂደት..... 12

2.4. አንብቦ መረዳትን በመማር ዙሪያ ያሉ አይታዎች፡ - ..... 15

2.5. የአንብቦ መረዳት ብልሀት ዓይነቶች..... 22

2.6. ማጠቃለል አንብቦ መረዳት ብልሀትን በመማር ሂደት የተማሪዎች ባህሪያት ያላቸውተጽዕኖ..... 24

2.7. የቀደምት ጥናት ቅኝት ............ 27
ምዕራፍ ሶስት ............ 30
የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ............ 30
3.1. የጥናቱ ንድፍ ............ 30
3.2. የናሙና አመራረጥ ............ 30
3.2.1. የትምርት ቤት አመራረጥ ............ 30
3.2.2. የተማሪዎች አመራረጥ ............ 30
3.2.3 የጥናቱ አካላይ ............ 31
3. 3 የመረጃ ማሰብሰቢያ ዘዴ ............ 31
3.3.1 ፈተና ............ 32
3.3.2 ቃለመጠይቅ ............ 33
3. 4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ............ 33
3. 5 የጥናቱ ሂደት ............ 34
ምዕራፍ አራት ............ 35
የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ............ 35
4.1. የውጤት ትንተና ............ 35
4.1.1. የፈተና መረጃ ትንተና ............ 36
4.1.2. የቃለ መጠይቅ ትንተና ............ 44
4.2 የውጤት ማብራሪያ ............ 45
ምዕራፍ አምስት ............ 47
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሔ ............ 47
5.1 ማጠቃለያ ............ 47
5.2 መደምደሚያ ............ 48
5.3 መፍትሔ ............ 49
ዋቢ ፅሁፎች ............ 49

የ ሠን ጠረዥ ማውጫ

# አጠቃሎ


የጥናቱ ዋና አላማ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡ የጥናቱ ንድፍ ከፊል ሙከራዊ ነው፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በምስራቅ ጎጃም በብቸና ከተማ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2011 ዓ.ም በ9ኛ የክፍል ደረጃ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙት 915 ተማሪዎች መካከል በእደል ሰጪ ናሙና ዘዴ የተመረጡ 60 የቁጥጥር ቡድንና 58 የሙከራ ቡድን በድምሩ 118 ተማሪዎች ናቸው፡ ከእነርሱም በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በዳግም ልኬት ናሙና ቲ–ቴስትና በነጻ ናሙና ቲቲስት ተሰልተው በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትነዋል፡፡ በውጤት ትንተናው መሰረት የሙከራ ቡድኑ የድህረ

ትምህርት ፈተና በቡድን አማካይ ውጤት በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት (p<0.05) ታይቷል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀትን ብቻ በመማራቸው የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ የተሻሉ መሆናቸውን በጉልህ አመላክቷል፡፡ በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የሚማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት መካከልም በስታትስቲክስ ጉልህ የሆነ ልዩነት (p>0.05) አላሳየም፡ በዚህም መሰረት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በማጠቃለል ብልሀት አንብቦ መረዳት ችሎታ ከሙከራ ቡድን የተሻሉ አለመሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የሆነው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ምንባብን በሚማሩበት ጊዜ የማጠቃለል ብልሀትን ብቻ በመማራቸው ነው፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1.የ ጥናቱ ዳራ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደሌሎች የትምህርት አይነቶች ሁሉ የራሱ የሆኑ አላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም ዓላማዎች መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) ማዳበር እና የስነ ልሳንና የስነ ፅሁፍ ዕውቀቶችን ማስጨበጥ ናቸው፡ ስለሆነም አላማዎችን ከግብ ለማድረስ በመማሪያ መፅሐፍት ውስጥ የሚካተቱት ይዘቶች ልዩ ትኩረትን ይሻሉ፡ አንብቦ መረዳት አንዱ የቋንቋ ትምህርት ይዘት እንደመሆኑ መጠን የቋንቋ ትምህርትን አላማ ያሳካ ዘንድ ተገቢ ይዘቶችን እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ሊኖረው ይገባል፡፡ እንዲሁም ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የመግባባት ተግባር የሚያጎለብት እንዲሆን ይጠበቅበታል፡፡

Grellet (1981) በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉም ክሂሎች እንዲዳብሩ ይፈለጋል፡፡ ከአራቱ መሰረታዊ ክሂሎች አንዱ የሆነው የማንበብ ክሂልን ለማዳበር መምህራን በይበልጥ በአጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡ በክፍል ዉስጥ የተማሪዎችን አቅም ለማሳካት በተለያዩ የትምህርት አይነቶች የሚዘጋጁ ፈተናዎች በዋናነት የንባብ ግንዛቤ አቅምን ይጠይቃሉ፡ የቀለም ትምህርትን ከሚዳት ባለፈ ክሂሉ ለተማሪዎች ከትምህርታቸው ዉጭ ከተለያዩ ጽሁፎች ጋር ጥሩ የሆነ ተግባቦት እንዲፈጥሩ ያግዛል፡፡

እንደ Carrell (1988) አገላለጽ ደግሞ ማንበብ በበርካታና ሰፊ ጽሐፍ ውስጥ ፀሐፊው ለፈደላትና ለቃላት፣ ለሐረጋትና ዓረፍተ ነገሮች የተጠቀመውን የትርጉም አሰጣጥ የምንገነዘብበት ሂደት ነው ይላል፡፡ Edaso Mulu ( 2007)፣ Biges,Entewen and Kirban (1988)ን ጥናቶች ጠቅሶ እንዳሰፈረው ማንበብ ከጽሑፎች መረጃ የማሰባሰብ ሂደት ነው ይላል፡፡ የመረጃ ሂደቱም ቅደምተከተል ያላቸው ስምንት ደረጃዎችን የጠበቀ መረጃን የማሰባሰብ ሲሆን የፊደል ቅርጽን፣ ፊደላትን፣ ድምፆችን፣

ቃላትን፣ የቃላትን፣ ትርጉም፣ ጽንሰሀሳቦችን፣ ዋና ሀሳቦችን እና ጭብጦችን ያካትታል በኢዳሶ አባባልም የፊደል ቅርጽን (Features) ፊደላቱ የተመሰረቱበት መስመር፣ ፊደላት (letters) የቅርፆች አመሰራረት ቅጦአዎማር፣ ደምፆች(sounds) *ፊደላት የሚወክሉትን ደምጽ፣ ቃላት (words) ፊደላቱ በአንድ ላይ ሆነው የሚወክሉ ደምፅ ትርጉም፣ የቃላት ትርጉም* (chunks) ቃላቱ የሚወክሉ አንድ ትርጉም ወይንም አባባሎች ቀለል ያሉ

አንብቦ መረዳትን የትርጓሜ ትውስታዎችን የምናከናውንበት መሆኑን ፣ጽንሰ ሀሳቦች (ideas) ቀጥተኛ ባይሆንም የጽሁፉን ሃሳብ መረዳት ፣ዋና ሀሳቦችን "main idea" የጽሁፉን ወካይ የሆነውን ሀሳብ ወይም ጠቅለል አድርጎ የያዘው ነጥብ /gist of the text/መሆኑንና ሃሳቦችና ዋና ሃሳቦች የትርጓሜ ፈጠራው አካሎች መሆናቸውን ከርባይ አብራርቷል፡፡ በተመሳሳይ ጭብጥ (Themes) በጽሁፉ ውስጥ ምን ለማለት እንደ ተፈለገ የትርጓሜ ስራ የሚወጣበት መሆኑ ተገልጧል፡፡

እንደ Tesfu (2015)፣ አገላለጽ ደግሞ ማንበብ በሁለት የተያያዙ ሂደቶች የተመሠረተ ሲሆን የቃላት ግንዛቤና አንብቦ መረዳት ናቸው ይላል፡፡ የቃላት እውቅና ወይም ግንዛቤ የተጻፉት ምልክቶች አንድ ሰው ከሚናገረው ቋንቋ ጋር ያላቸው የስርጸት ሂደት ነው፡ አንብቦ መረዳት ደግሞ በጽሁፍ ውስጥ ያሉትን ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም መረዳት መሆኑን ጠቅሷል፡፡

Grellet (1981)፣ አንብቦ መረዳት በጣም አስፈላጊ የሆነ የቋንቋ መማሪያ ንዑስ ክህሎት ነው፡ በዚህም የተነሳ ለተማሪዎቻችን በአግባቡ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ብቃትና ችሎታ፣ ለትምህርታቸው ስኬታማት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡ ይህ ብቃት ወይም ችሎታ ደግሞ የጽሁፉን ዋና ሃሳብ ፣ የተወሰኑ መረጃዎችን፣ ያልተለመዱ ቃላትን ትርጉም ወይም አባባሎች፣ ማጣቀሻዎች መስባሰብን፣ የፀሐፊውን ዓላማ መረዳትንና ፅሁፉን ማገምገም የሚያካትት መሆኑን ዘርዝሯል፡፡

እንደ USAID (2016)፣ አንብቦ መረዳት ማለት ከቴክስት ትርጉም የሚወጣበት ንቃተ አካል ሂደት እና አንባቢ ከጽሑፍ ትርጉም የሚያወጣበት ተራክቧዊ ሂደት ነው። በዚህም ሁለት ዓይነት የመረዳት ክሂሎች አሉ። እነሱም ቀጥተኛና አንደምታዊ ይባላሉ፤ ቀጥተኛ መረዳት ማለት በጽሑፉ በቀጥታ የተገለጸን ሀሳብ ማወቅ ማለት ነው። ይህ ዓይነቱ ሀቅን ወይም እውነታን የማስታወስ ወይም መሰረታዊ ግንዛቤ የማግኘት

ችሎታ የሚጠይቀው ቀላል ክሂልን ነው፡፡ በሌላ በኩል አንደምታዊ መረዳት ከተባለው በማሳት ያልተባለውን ማውጣት ወይም በአንደምታ ለመረዳት የቋንቋ እውቀትን መጠቀም ማለት ነው፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ተማሪዎችን ለማገዝ የሚያስችሉ በርካታ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አሉ በማለት ያስረዳል፡፡

የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች፣ Pardo (2004)፣ ገለጻ መሰረት ጥሩ አንባቢያን ጽሁፎችን የሚገነዘቡበት አእምሮአዊ ሂደት ነው፡ እነዚህንም ብልሀቶች ለአንባቢዎች በግልጽ በማስተማር ጽሑፎችን ትርጉም ሰጥተው እንዲያነቡ ማድረግ ይፈለጋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ሂደቱ ንባብ

ከመጀመሩ በፊት የሚጀምርና ከንባብ በኋላም የሚቀጥል ነው፡ ጥሩ አንባቢያን የቅድመ ንባብ አሰሳዎችንና ከንባብ በኋላ ያሉ ማጠቃለሎች ጨምሮ በርካታ ብልሀቶችን በንባብ ጊዜ ይጠቀማሉ፡፡ Harvey and Goudvis (2000)፣ እንደገለጹት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች፡ ቅድመ ዕውቀትን ማንቃት፣ መከታተልና ግልጽ ማድረግ፣ መተንበይ/መገመት/፣ ጥያቄዎችንና ማጠቃለያዎችን ማዘጋጀት የሚሉትን ዘርዝረዋል፡፡

Edaso Mulu (2007)፣ Encychlopidia (1992)ን፣ Langan (2003)ን፣ Nuttall (1982)ን፣ Anadorkin (1974)ን፣ ጠቅሶ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ውስጥ አንባቢዎች ከሚያውቁት ቃል ጥግ ያሉ ፍንጭ ሰጪ አባባሎችን በመጠቀም፣ የቃላትን ሰዋሰዋዊ አገባብ በመጠቀም፣ የቃላትን ቅድመ ቅጥያ፣ ድህረ ቅጥያ እና ዋና ግስ በመጠቀም አንብቦ መረዳትን ማዳበር እንደሚቻል አብራርቷል፡፡

ማጠቃለል ማለት ዋናውን ጽሁፍ በማሳጠር በጣም አስፈላጊ ነጥቦችን፣ ዋና ዋና ሃሳቦችን፣ አስፈላጊ ዝርዝሮችን ብቻ የያዘ ከዋናው ጽሑፍ ጋር በይዘቱ ተመሳሳይ የሆነ ጽሁፍ ነው፡ በማጠቃለል አላስፈላጊ መረጃዎችን በማስወጣትና አጠቃላይ ሃሳብን በመጠቀም የሚከናወን ተግባር መሆኑን Denton and etal (2007)፣ ገልጸዋል፡፡ በDentonን አገላለጽ ስድስት ደረጃዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡ ዋና ዋና

ሃሳቦችን ማቅረር፣ አስፈላጊ ነጥቦችን ማስመር፣ የሚያስፈልጉትን ማያያዝ፣ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ ማጠቃለያውን ማጻፍና ማጠቃለያውን ማከለስ/ማሻሻል ናቸው፡

ማጠቃለል አንድን በዝርዝር ተለጥጦ የቀረበ ጽሁፍ በማንበብ ሃሣቡን በታመቀና በተመጠነ መልኩ ለማቅረር የሚያስችል የአንብቦ መረዳት ብልሀት ማጠቃለል ይባላል ሲል Oxford (1990)፣አብራርተዋል፡፡ የጽሁፍን ዋና ዋና ሀሣቦች ለይቶ ማውጣትን የሚጠይቀው ይህ ብልሀት የማንሻ ጽሁፉን ይዘት እንዳለ በመጠበቅ በቅርጹ ላይ ሰፊ ማሻሻያ ማድረግን ይፈልጋል፡፡

አንድን ጽሁፍ ለማጠቃለል፣ የማጠቃለል ብልሀትን በመጠቀም ተማሪን ማለማመድ እንደሚገባ Armbruister and etal (2002)፣ጠቁመዋል፡፡ ከስልቶች ውስጥ የጽሁፉን መዋቅር መሰረት ያደረጉ ቁልፍና የአጠቃላይ ሀሣቡን የሚመለክቱ ቃላትንና ሀረጋትን ማሥፈር፣ በመሪ ቃላቱና ሀረጋቱ ሥር የሚነተቱ ሀሳቦችን ማለየት፡፡

ሌላው የማጠቃለል ብልሀት እርከናዊ አጠቃሎ (Hierarchical summary) Tayler and Bich (1984)ን፣ Tayler and Berkoywites (1980)ን፣ በመጥቀስ Armbruister and etal (2002)፣ አስረድተዋል፡፡ በዚህም ርእሶቹን፣ ንኡስ ርዕሶቹን እና አንቀጾቹን መሰረት አድርገው ንድፍ ማዘጋጀት፤ በመቀጠልም በየርእሶቹ፣ በየንኡስ ርእሶቹና በየንቀጾቹ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሀሣቦችን ለይቶ ማውጣት፡፡ በመጨረሻም ዋና ዋና ሀሳቦች መሰረት በማድረግ አንድ መሪ ሀሣብን በመፍለቅ በመሪው ሀሣብ ስር በማስተሳሰር የምንባቡን ጠቅላላ ሀሣብ ማጻፍ የሚሉ ናቸው፡ Birawon and Diay(1983) Rahert(1986)፣ዋቢ በማድረግ Armbruister and etal (2002)፣ እንደጠቀሱት አላስፈላጊ መረጃዎችን፣የተደጋገሙ መረጃዎች ከሚበበው ጽሁፍ ውስጥ ካሉ መሰረዝ፣ ክፍፍልን የሚያሳዩ አገላለፆችን አጠቃላይነት ባላቸው ቃላትና ሀረጋትን በመተካት ማጠቃለል፣ በጽሁፍ ውስጥ

የተገለጹ ሀይለቃሎች ወይም ዋና ሃሣቦች ካሉ እንደሚ ሀሣብ አደርጎ መጠቀም፣ ጸሀፊው የየአንቀጹን ዋና ሀሣብ በኃይለቃል ሚልኩ ያላሰፈረ ከሆነ በአንባቢው በኩል የራስን ሀይለቃል መፍጠር ናቸው፡

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን የምህራን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ የዚህ ጥናት ትኩረት የተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ በማጣራት ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር

በዚህ ጥናት ለመዳሰስ የተሞከረው ዋና ጉዳይ የተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ መፈተሽ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አጥኚው መረጃዎችን ከመዳሰስና ካለው የማስተማር ልምድ አንፃር ያጋጠሙትን መነሻ ምክንያቶች ለማየት ሞክሯል፡፡

የመጀመሪያው አነሳሽ ምክንያት በአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ በ2007 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ያለው የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ በሁሉም ምዕራፎች እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ላይ የማጠቃለል ብልሀትን ተማሪዎች በተለያዩ አግባቦች እንዲሞክሩ የአማርኛ ቋንቋ መምሪያ መጽሀፍ አምስተኛ ክፍል (ከገጽ 21-23) ይጠይቃል፡፡ ይህም ሲታይ ሀሳቡ አዲስና ጠቃሚ ሀሳብ በመሆኑ ለማስተማሩንም ቢሆን አዲስ ሀሳብ በመሆኑን ስልጠና በምንሰጥበት ወቅት ከሚነዘሩ ሀሳቦች ለመረዳት በመቻሌ እና በ2004 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መፅሐፍ ለዚህ ብዙም ትኩረት ያልሰጠ በመሆኑ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የተደረጉ ጥናቶችን በማሰስበት ጊዜ የተጠኑ ጥናቶች ተቀራራቢ እንጂ ተመሳሳይ ጥናት ለማግኘት ባለመቻሌ ነው፡ በመሆኑም በውጭ አገር የተጠኑ ጥናቶች ያላቸውን አማካከትና ጎራ በመዳደስ ያለውን መነሻ ለማየት ሞክሯል፡፡ ይኸውም -

የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ የሚያሻሽል ብልሀቶች ትምህርት በማገዝ ማስልበት አስፈላጊ መሆኑ ይገለጽ እንጅ Langer and Mulasie (1988)፣ በማጣቀስ Conley (1992)፣ እንዳሰፈሩት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ተፈላጊ ደረጃ ላይ ሳይደርስ ይቀራል፡፡ ለዚህም እንደአንድ ችግር የሚቀሰው መምህራን ክሂሉን ሲያስተምሩ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በተገቢው መንገድ አለማለማመዳቸው እነደሆነ ነው፡ ይህንን ሀሣብ የሚያጠናክረው Noturn (1997)፣ የጥናት ውጤቶች የሚያሣዩት በአንብቦ መረዳት ትምህርቶች ውስጥ ተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሞዴል ማድረግና መግለጽ ወይንም ማብራራት ችላ ማላቸውን ነው፡ በማለት በማስተማር ሂደቱ ዙሪያ ችግር መኖሩን ማጠቆማቸው ነው፡

የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በመማር አስፈላጊነት ዙሪያ የሚስማሙ ፀሀፍት ቢኖሩም ብልሀቶችን በማስተማሪያ መንገዶች ላይ ግን የተለያዩ ሀሣብ አላቸው፡ በተለይም ብልሀቶችን በግልፅ በማስተማርና ባለማስተማር መካከል የተለያየ ሀሣቦች ሲሰነዘሩ ይስተዋላሉ፡ ለአብነትም Brown and Others (1986)፣ Plisar and Brown (1984)፣ Wnstien and Mayer (1986)፣ Winglande and Haline (1988) በማጣቀስ O'Malley and Chamot (1990) እንደገለፁት ተማሪማሪዎቹ የመማር ብልሀቶቹን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ በግልጽ ማስተማር እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

አጥኝው ከዚህ በላይ የተነሳውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በሀገር ውስጥማለትም በአማርኛ ቋንቋ አፈፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከላይ ከተሰነዘሩት ሀሳቦች ወይም በሁለት ከተነሱት ጎራዎች አንፃር የሚያሻሽል ብልሀት በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ እስፈላጊ ነው ወይም አስፈላጊ አይደለም የሚለትን የተሰነዘረ ሀሳብ በሚፈተሽ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ላይ የሚያሻሽል ብልሀት ምን ይመስላል የሚለውን ለሚፈተሽ ተነሳስቷል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ይህንን ጥናት ለማካሄድ የተነሳሳው የዚህ ጥናት አጥኝ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጀ ትምህርት ቤት ባስተማረባቸው ረጅም አመታት ከተለያዩ ትምህርት ቤት የቋንቋ መምህራን ጋር በመወያየት ባገኘው ዕድል ብዙ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር እንዳለባቸው መረዳት

ችሏል፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የትምህርት አሰጣጡ ተማሪ ተኮር ወይም አሣታፊ የትምህርት አሰጣጥ እየተበረታታ በመምጣቱ ብዙ የአማርኛ መምህራን ለተማሪዎች ማስታወሻ /note/ አዘጋጅተው በማፋ ላይ አያተኩሩም ወይም ኖት አይሰጡም፡ ከዚህ ይልቅ በራሳቸው ተማሪዎች የመማሪያ መፃህፍትን እያነበቡ ከየምንባቦች የተረዱትን ፍሬ ሃሳብ በደብተር እንዲያሰፍሩ፣ የክፍልና የቤት ሥራዎችን እንዲሰሩ፣ ምንባቦችን እንዲያሳጥሩ ወይም እንዲያስፋፉ፣ ማጠቃለያዎችንና፣ ማስታወሻ እንዲፅፉ፣ ይደረጋል፡፡ ይህም አንዱ ተግባራቸው እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ ይህን ለማድረግ ሲቸገሩ ይታያል፡፡ ኖት የሌላቸው በርካታ ናቸው፡ መምህር ሲያሰተምሮም ማስታወሻ አይዙም፡ አንብቦ የሚረዳት ችግር አለባቸው፡ ምንባቦችን ካነበቡ በኋላ ሰለምንባቡ የተጠቃለለ ሀሳብ የማቅረብ ችግር አለባቸው፡ ብሎም ችሎታ ካላቸው ከተወሰኑ ተማሪዎች ደብተር እየተዋሱ ሲገለብጡ ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ ከሌሎች ሲገለብጡ ከነስህተቶች በማልበጥ የተዛባ አረዳድ ይታይባቸዋል፡፡ አንዳንዶችም ችሎታው የሌላቸውና የሚዋሱት ያጡ ምንም ዓይነት ማስታወሻዎች የሌላቸው ናቸው፡

በአጠቃላይ ከላይ እንደተጠቀሰው እንደ አጥኙው ዳሰሳ ፣ የማጠቃለል ብልሀትን መማር አስፈላጊነት የሚጠሙ ጸሀፍት Lunzer and Gardner (1979)፣ እንዳሉ ሁሉ በዚህ ሀሣብ

የሚያስማሙ ጸሀፍት Doll and Others(1991)፣ ሞራቸውን በማንዘብ ፣ የብልሀቱን መማርና ስኬታማት ከባህል ባህል ማእያየቱ ከሀገራችን አወድ አንፃር ሚያተሸ አስፈላጊ መሆኑ፤ የማጠቃለል (summarizing) አንብቦ ሚዳት ብልሀትን ማዋርና አለመማር ከተማሪዎች የአንብቦ ሚዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና በሚፈተሸ በጉዳዩ ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱ ሁነኛ ምክንያቶች ናቸው፡ እነዚህንም ችግሮች በጥናቱ ለሚፈተሸ ጥናቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡

1. የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ የሚረዳት ችሎታን ለማልበት ያለው ሚና ምን ይመስላል?

## 1.3. የ ጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የማጠቃለል ብልሀትን የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሻሻልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ለዚህም ተግባር ማስፈጸሚያ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ቀርበዋል፡፡

1. የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ ለመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለውሚና መመርመር፡

## 1.4. የ ጥናቱ አስፈላጊነ ት

ይህ ጥናት ከላይ ለቀረቡ መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ለተማሪዎች፣ ለቋንቋ መምህራን፣ ለስርዓተ ትምህርት አዘጋጆችና ለተመራማሪዎች የሚከተሉትን ጉዳዩችን ከማስገኘት አንፃር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

- ለተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀትን እንዴት አድርገው ቢለማመዱና ቢጠቀሙ የማጠቃለል ችሎታቸው ከፍ ሊል እንደሚችል አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡
- ለቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የማጠቃለል/summarizing/ ብልሀትን በግልጽ በማስተማርና ባለማስተማር መካከል የሚኖረውን ፋይዳ በማንዘብ የተሻለ አማራጭ የሚሆን አቅጣጫ በተግባር የተማሪዎችን ችሎታ ለማሻሻልበት ጥረት እንዲያደርጉ ጥቆማ ይሰጣሉ፡፡
- ለስርዓተ ትምህርትና ለማህፍት አዘጋጆች የማጠቃለል የአንብቦ መረዳት ብልሀትን እንዴት ባለ ሁኔታ በዝግጅታቸው ውስጥ አካቶ መቅረብ ለተማሪዎ የአንብቦ መረዳት ማሻሻልበት እገዛ እንደሚያደርጉ ጥቆማ ይሰጣል፡፡
- ለተመራማሪዎች በማጠቃለል / summarizing / የአንብቦ መረዳት ብልሀት አቀራረብ ዙሪያ እንዲሁም ማጠቃለል ይህን የአንብቦ መረዳት ብልሀት ከተለያዩ የተማሪዎች ባህሪያት አንፃር በሰፊው ለማጥናት ለሚሹ መነሻ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 1.5. የ ጥናቱ ወሰ ን

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማራ ክልል፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን፣ በብቸና ከተማ ነው፡፡ ጥናቱ በወረዳው ከሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ተከናውኗል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የአጥኝው የስራ ቦታ በመሆኑ ለጥናቱ አመቺ ስለሆነ ነው፡

በመሆኑም ሌሎች የማግስት እና የግል ትምህርት ቤቶችን አያካትትም፡ ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በ2011 ዓ.ም በበላይ ዘለቀ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል በመማር ላይ ባሉት ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡ ዘጠነኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በመሆናቸው ሚናዎችን በተገቢው ማገድ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነባቸው ነው፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በበላይ ዘለቀ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡ በተጨማሪም ጥናቱ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የማጠቃለል ብልሃት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማፈተሽ ነው

## 1.6. የ ጥና ቱ ወሰ ን ነ ት

ይህ ጥናት በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በእነማይ ወረዳ በብቸና ከተማ በላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ የሚመረምር ሲሆን ጥናቱ የሌላ ዞን እና ወረዳ እንዲሁም በወረዳው ውስጥ ያሉ ሌሎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን በጥናቱ ናሙናዎችን ከጊዜ፣ ከገንዘብ እና ከጉልበት እጥረት የተነሳ ያካተተ ባለመሆኑ ውስንነት አለው፡

## 1.7. የ ምር ምሩ ቁል ፍ ቃላ ት ብያ ኔ

**አንብቦ መረዳት** – በጽሁፍ ውስጥ ያሉትን ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች የሚያስተላልፉትን መልዕክት መረዳት ማለት ነው፡

**የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች** – አንባቢያን ጽሁፎችን የሚነዘበቡበት አእምሮአዊ ሂደት ነው፡

**የማጠቃለል ብልሀት**– አንድን በዝርዝር ተለጥጦ የቀረበ ጽሁፍ በማንበብ ሃሳቡን በታማቀና በተማከነ መልኩ ለማቅረብ የሚያስችል የአንብቦ መረዳት ብልሀት ማጠቃለል ይባላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1. የማኅበብ ምንነት

ማኅባብ ሁሉንም የሚያስማማ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ የሌለዉና እንደሁኔታዉ በተለያየ መንገድ ብያኔ ሲሰጠዉ የሚቢተዋል እንደሆነ Simith (1985)፣ ይገልጻሉ። ምክንያቱም ይላሉ Simith ማኅባብ የሚያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ስነልቦናዊና አእምሯዊ የሆኑ ዉስብስብ ነገሮችን አዋህዶ የያዘ የአካላዊና አእምሯዊ ቅንጅት ተግባር በመሆኑ ነዉ። ማኅባብ በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች ቢሰጡትም የብያኔዎቹ የትኩረት አቅጣጫ ግን ጽሁፍን አንብቦ ከሚዳት፣ ሚጃን ከመቀበል፣ በንግግር የሚቀርብ ሚልክትን በጽሁፍ ከማግኘት አኳያ የሚያጠነጥኑ እንደሆነ Nuttal (1982)፣ ይገልጻሉ።

እንደ Nuttal(2000)፣ አገላለጽ ማኅበብ ጸሀፊው በስራዉ ዉስጥ ያሰፈረዉን ቁም ነገር ለሚዳት አስፈላጊ ሚጃን ከዉስጥ ለይቶ ለማዉጣት የጸሀፊዉን ሀሳብ ይምሚምሯል። ስለዚህ ማኅበብ የሌሎችን

ሃሳብ ለሚረዳት እንዲሁም ለመገባበት የምጠቀምበት ተግባር ነዉ፡ Tesfu (2015)፣ Devis (1995)ን፣ በመጥቀስ እንደገለጹት ደግሞ ማንበብ ግላዊ ነዉ፤ ማንበብ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚኙ የአንድ ጸሀፊ መልእክት በመከተል ምላሽ ለመስጠት የምንጣከርበት አዕምሯዊ ተግባር ነዉ፡ በማያዝም ማንበብ ግላዊ በመሆኑ የአነባበቡን ሂደትና ለጸሀፊዉም የሚሰጠዉን ምላሽ በቀጥታ ላናስታዉስ እንችላለን ይላሉ፡፡

በሌላ መልኩ Harmer (1991) እንደሚገልጹት ማንበብ በተቀባይ ክሂሎች ዘርፍ የሚካተት ሲሆን ከምኛነበዉ ጽሁፍ ዉስጥ ቁም ነገሩን ነቅሶ ማዉጣትን፣ የምንባቡን ዝርዝር ሃሳብ መረዳትን አጠቃልሎ የያዘዉ መሆኑን ያሳክታል፡፡ በዚህም መሰረት ንባባ በአንድ ጽሁፍ ዉስጥ የቀረበን ቁምነገር አንብቦ ለመረዳት የሚደረግን ጥረትና የአንባቢዉን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ከጸሀፊዉ ወደ አንባቢዉ መልእክት የሚተላለፍበት ዘዴ ነዉ፡

## 2.2. የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት ሲባል በጽሁፍ ዉስጥ ሊተላለፍ የተፈለገዉን መልእክት በተቻለ መጠን ማንዘብ ነዉ፡ በሌላ አባባል የሚፈለገዉን መረጃ ከአንድ ጽሁፍ ዉስጥ ፈልቅቆ ማዉጣትን የሚጠይቅ ነዉ፡ አንባቢዉ በተገቢዉ ፍጥነት የሚፈልገዉን መረጃ የሚያወጣበት የሚፈለገዉንም የሚረደበት ጥልቅ ግንዛቤ የሚያካከትበት ዘዴ ነዉ William (1984)፡፡ እንደ GreenWood (1981)፣ አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሁፍ ዉስጥ ሊተላለፍ የፈለገዉን መልእክት ማንዘብ ነዉ፡ በእርግጥ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ሊለያይ ይችላል፡፡ይህም ከሚነበበዉ ነገር፣ ከሚበነበት ዓላማ ከአነባበብ ዘደዉ ማለያየት ሊከሰት ይችላል Nattual (2000)፣Smith (1985)፣ እንደሚሉት ደግሞ አንብቦ መረዳት አንባቢዉ ይዞት ለሚሳዉ ጥያቄ መልስ ማግኘት ማለት ነዉ፡ አንባቢ ለጠየቀዉ ጥያቄ መልስ አገኘ ማለት በአንባቢዉና በጸሀፊው መካከል በአንብቦ መረዳት ተግባቦት መኖሩን ያሳያል፡፡ በአጭሩ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ምንባብ ዉስጥ የሚፈለገዉን መረጃ ለይቶ ማዉጣት መቻል ነዉ ልንለዉ እንችላለን፡፡

እንደ Grellet(1981) አገላለጽ አንብቦ መረዳትን በሁለት ከፍለን መመልከት እንችላለን፡፡አንደኛዉ በምንባብ ዉስጥ በግልጽ የሰፈሩ ጉዳዩችን ማንዘብ ነዉ፡ በስሩም በጽሁፍ ዉስጥ የቀረቡትን ዋናዋና

ሃሳቦች ማንዘብ፣ በግልጽ የሚታዩ ሁኔታዎችን፣ ክስተቶችን፣ ድርጊቶችን ወዘተ ቅደምተከተል ማስታወሻ፣ ግልጽ የሆኑ አንድነቶችንና ልዩነቶችን ማየት፣ የምክንያትና ዉጤት ማስናከል ማስታወስ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ደግሞ ተማሪዎች ተጠየቃዊ እዉቀትንና ግምትን በመጠቀም በጽሁፍ ዉስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ሃሳቦችን አንብበዉ የሚረዱበትን ሁኔታ ይመለከታል፡፡ ይህን መሰል አንብቦ መረዳት ካሉት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን ጭብጥ ማየት፣ ደጋፊ ጽሁፎችን ለይቶ ማውጣት፣ ከምክንያትና ዉጤት ጥብቅ ትስስር የተነሳ ቀጣዩን ነገር መገመት፣ በምንባቡ ዉስጥ በይፋ የሰፈረን ፍንጭ በመጠቀም የገጸባህርያትን ባህሪና የደራሲዉን የቋንቋ አጠቃቀም መረዳትን ያካትታል፡፡ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለዉ አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሁፍ ዉስጥ የሚገኙ ቃላትን ከማንዘብ ባሻገር ጠቃሚ መረጃዎችን ለይቶ ለማዉጣት የሚያስችለንን ሁኔታ ያጠቃልላል፡፡

## 2.3. አንብቦ መረዳትን የማስተማር ሂደት

ሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ትምህርት የታለመላቸዉን ግብ እንዲመቱ በመስኩ ጥናት ያደረጉ መምህራን የተሻለ ነዉ የሚሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች እና ሂደቶች ያቀርባሉ፡፡ለዚህም ጌታቸዉ (1996)፣ አዜብ (1984)፣ በመጥቀስ´´የአንድ መምህር ዉጤታማ የማስተማር ተግባር መለኪያዎች መካከል የቀረበለትን መሰረታዊ የማስተማሪያ ዘዴ እና ሂደት ተከትሎ በክፍል ዉስጥ ማስተማር ነዉ በማለት ገልጸዋል፡፡’’ በመሆኑም አንብቦ መረዳትን በክፍል ዉስጥ ለማስተማር ልንከተላቸዉ የሚገቡ ተግባራትን እንደሚከተለዉ እንመለከታለን፡፡

**ቅድመ ንባብ ተግባራት፡ –** ይህ የቅድመንባብ ተግባራት አቀራረብ ሁለት ዓብይ ዓላማዎች አሉት፡፡እነርሱም ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ምክንያት በመግለጽ የማንበብ ፍላጎታቸዉን ማነሳሳትና ስለምንባቡ ይዘት መነሻ ሃሳብ እንዲኖራቸዉ ማስቻል ነዉ ጌታቸዉ (1996)፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነበቡበት ዓላማ ሊገለጽላቸዉ ይገባል፡፡ይህም ምንባቡን ምን ያህል ጠለቅ ብለዉ ማንበብ እንደሚገባቸዉ ይጠቁማል፡፡ በዚህ አቀራረብ መሰረት ተማሪዎች ጽሁፍን ወደማንበብ ተግባር ከመሸጋገራቸዉ በፊት ከእርእሱ ጋር በተያያዘ ሚለኩ ሀሳብ እንዲሰነዝሩ ጥያቄዎችን በማቅረብ ማነሳሳት በምንባቡ ዉስጥ የሚገኙ ለንባብ እንቅፋት ይሆናሉ ተብለዉ የሚገመቱ ቃላትን ወይም ሐረጋትን ፍችዎች እንዲረዱ የሚደረግ

ተግባራትን ያካትታል Nuttal (1982)፡፡ ተማሪዎችም ለእንደነዚህ መሰል ጥያቄዎች ከቀደሞ ዕዉቀታቸው በማሳት አንዳንድ ሀሳቦችን በማስንዘር ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ ፍጹም ሆኖ አይታያቸዉም Stateman (1981)፡፡ በሌላ መልኩ ተማሪዎች ምን እንደሚያነቡ ለቀጣይ ደረጃ (የንባብ ጊዜ) ተግባራትን ማስተዋወቂያ ነዉ Me Donugh and Shaw(2003)፡፡ በጥቅሉ ተማሪዎች በዚህ ደረጃ፡ –

- ለንባብ በቀረበዉ ርዕስ ዙሪያ የግንዛቤ ጥያቄዎችን በማቅረብ በቅድመ ዕዉቀታቸዉ እንዲመልሱ በማድረግ ያነቃቃል፡፡
- ምንባቡን ለምን እንደሚያነቡ በማስተዋወቅ የማንበብ ፍላጎተቸዉን ይቀሰቅሳል፡፡
- የምንባቡ ይዘት ስለምን ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የቅድመንባብ ክንዋኔዎችና ጥያቄዎች ዋና ትኩረት ተማሪዎቹ የሚያነቡትን ምንባብ በጥሩ ሁኔታ እንዲረዱና ፍላጎታቸዉ እንዲነቃቃና ቅድመ ንባብ ቅንጫቢና ሚዜ ጥያቄዎችን ተመርኩዘዉ ስለምንባቡ ሀሳባቸዉን ይገልጻሉ፡፡

**የንባብ ጊዜ ተግባራት፡ –** በዚህ የንባብ ጊዜ ለትምህርት የቀረበዉ ምንባብ በተማሪዎች የሚነበበት ነዉ፡ ስለሆነም ተማሪዎች ምንባቡን አንብበዉ በማሉ ንቃተህሊና በማንዘብ አስተያየት እንዲሰጡ መምህሩ ያበረታታል Wallas (1992)፡፡ ብዙዎቹ ምሁራን Green wood (1981)፣ Nattual (1982) እንደሚሉት አብዛኛዉን ጊዜ ተማሪዎች ለትምህርት የቀረበዉን ምንባብ በጸጥታ እንዲያነቡ ይመረጣሉ፡ በአጠቃላይ መምህራን በንባብ ጊዜ ወቅት የአጠቃላይ ክፍሉን ሁኔታ የመቆጣጠር ተግባር እየተወጡ ተማሪዎች፡ –

- የጽሁፉን ዓላማ እንዲረዱ ማድረግ
- የጽሁፉን ይዘት እንዲረዱ ማድረግ
- የተለያዩ የንባብ ዓይነቶችን እንደየሁኔታዉ እንዲጠቀሙ ማድረግ
- ተማሪዎች ምንባብ ሲያነቡ ደቂቃ ወስኖ መስጠት የሚሉትን ጉዳዮች ከግምት ዉስጥ እንዲያስገቡ ማድረግም ይጠበቅባቸዋል በማለት Williams (1984) ሲገልጹ ተማሪዎችም በጊዜ ንባብ ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት፡ –

- በየአንቀጹ ጠቃሚ የሆነዉ ሃሳብ የትኛዉ እንደሆነ ማየት፣
- የምንባቡን ዋና ዋና ነጥቦች በወረቀት ወይም በህሊናቸዉ መመዝገብ
- አንብበዉ ሲጨርሱ በትክክል ያልተረዱት ሀሳብ ካለ ተመልሰዉ ዝርዝር ሀሳቦችን መመርመር ማክናወን ይጠበቅባቸዋል

**ደህረ ንባብ ተግባራት፦** – በዚህ የደህረ ንባብ ተግባራት ለትምህርት የቀረበዉ ምንባብ በቋንቋ ትምህርት ትርጉም የሚያገኝበት ጊዜ ነዉ በማለት Green Wood (1981) ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ያነበቡትን ንባብ የበለጠ እንዲገነዘቡ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ እንዲመልሱና ዉይይትም እንዲያከሂዱ ማድረግ ዋነኛዉ ትኩረት ነዉ፡የጥያቄዎቹ ዋና ዓላማም የተማሪዎችን አንብቦ ሚዳት ችሎታ ማጎበር ነዉ Green Wood (1981)፡፡ በሌላ መልኩ Lindsay (2006)፣ እንደሚሉት በደህረ ንባብ ደረጃ የማህራን ተግባር፡ –

- የምንባቡን ሀሳብ ሚዳት መቻላቸዉን ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎች ያቀርባሉ
- ምንባቡን እንዲገመግሙ ያበረታታል
- የምንባቡን ሃሳብ ለሚዳት ከራሳቸዉ ገጠመኝ ጋር እንዲያዛምዱ የሚረዱ ክንዋኔዎችንና
- እንደ ምንባቡ አመቺነትና መሻነት ተማሪዎች ንግግር እንዲያዘጋጁ የሚደርጉ ተግባራትን ያዘጋጃሉ፡

በዚህ የንባብ ደረጃ ላይ ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ በአነበቡት ጽሁፍ ላይ በጥልቀት በመወያየት ለንባብ በቀረበዉ ጽሁፍ ጥያቄዎችንና ዋና ዋና ጉዳዮች በቡድን የሚወያዩበት ክፍል ነዉ፡ይህ ሂደት ደግሞ እያንዳንዱ ተማሪ የመለሰዉን መልስ ለምን እንደሚሰጡ የሚረዳት ዕድል ይሰጠዋል፡፡ በዚህም ዕድል መምር አንድን ምንባብ አንብበዉ ምን ያህል እንደተረዱት ጥያቄዎቹ በሚሰሩበት ወቅት የት ላይና እንዴት እንደተሳሳቱ ሊያዉቁ ይችላሉ Nattual (2000)፡፡

### 2.4. አንብቦ መረዳትን በመማር ዙሪያ ያሉ እይታዎች፡ -

አንብቦ መረዳትን በመማር ዙሪያ በየዘመኑ የተለያዩ እይታዎች ሲንፀባረቁ ተስተውለዋል Notorn (1997)፣ Heilman & Others (1998)፣ Block (1997)፣ Doll & Others (1991)፡፡ እነዚህ ፀሃፍት እንደሚጠቁሙት ስለማንበብ የተለያዩ እይታዎች ካንፀባረቁ ንድፈ ሀሣቦች የባህሪያዊያን፣ የአዕምሯዊያን፣ የመስተጋብራዊያንና የዳራዊ (schemata) ንደፍ ሀሣብ ይገኙበታል፡፡ እንደ Heilman & Others (1998)፣ Notorn (1997) አገላለጽ ቀደም ባለው ጊዜ በባህሪያዊያን ንድፈ ሀሣብ (Behaviorist view) መሰረት ማንበብ የፅሁፈውን መልዕክት ለቅሞ ወይም ኮርጆ መልሶ እንደገና መስተጋባት እንደሆነ ይታሰባል፡፡ በዚህም እሳቤ መሠረት አንባቢው የማንበብ ተግባሩ ንቁ ተሳትፎ ሳይሆን የጸሀፊውን ሀሳብ የሚያስተጋባ አካል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

በአዕምሯዊያን ንድፈ ሀሣብ እሳቤ/ cognitive view/ መሠረት ግን ማንበብ እጅግ ውስብስብ አዕምሯዊ ሂደትን የሚጠይቅ ንቁ ክሂል በመሆኑ በጸሀፊው የሰፈረውን ሀሳብ በመልቀም ላይ ብቻ የሚተኩር ሲሆን ከራስ ገጠመኝ ጋር እያዛመዱ ምላሽ መስጠትን የሚሻ ክሂል እንደሆነ ይታሰባል Block(1997)፣ Doll & others (1991)፣ በመሆኑም አንብቦ መረዳት መልዕክትን ከመቀበል ባለፈ ትርጉም መመስረትን ወይም መፍጠርን መሠረት ያደረገ ነው፡

Yaris and Hodgisen (1995)፣ ዋቢ በማድረግ Heilman & Others (1998)፣ እንደሚያስረዱት ደግሞ ዳራዊ ንድፈ ሀሳብ / schema theory/ መሠረት፣ አንብቦ መረዳት በአዲስ እውቀትና በቀደም እውቀት መካከል በሚፈጠር ውህደት የሚገኝ ውሶት ነው፡ ይህም

ማንበብ በቴክስቱ ውስጥ የሚኙ ገጽታዎችንና አንብበው ትርጉም በመፍጠር ላይ ያለውን ቀደምት እውቀት የማስተሳሰር ብቃትን የሚጠይቅ መሆኑም የሚጠቁም ነው፡

በመስተጋብራዊ ንድፈ ሀሳብ /interactive theory/ መሠረት ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሁፍ ለመረዳት ከራሳቸው ጋር ከተያያዙ ግላዊ ሁኔታዎች፡ ከሚያነቡት ቴክስትና ንባቡን ከሚፈጽሙበት አውድ ጋር ዘርፈ-ብዙ የሆነ መስተጋብር ይፈጥራል Heilman & Others (1998) ፣ Notorn

(1997)፡፡ ለዚህም በወሳኝነት የሚሄዱት የአንባቢው ቀደምት እውቀትና የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ከቴክስቱ ጋር አቀናጅቶ የመጠቀም ሁኔታዎች እንደሆን ይጠቁማሉ፡፡

አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት አንባቢው በጊዜው ከሚገኝበት እውቀት በተሻለ የተሻሉ የማንበብ ብልሀቶችን ተገንዝቦ የጽሁፉን መልዕክት ለሚፈተሽ መጠርና መረዳቱን በራሱ ለመቆጣጠር መማር እንደሚገባው Doll & others (1991) ያስገነዝባሉ፡ አንብቦ መረዳት ቀደምት እውቀትንና ከቴክስቱ የሚገኝ አዲስ እውቀትን ወይም መልዕክትን ማዛመድ ብሎም መረዳትን ለማጎልበት፣ለመቆጣጠርና ለረጅም ጊዜ ለማቆየት የሚያስችሉ ብልሀቶችን አጣምሮ መተግበርን የሚጠይቅ ስለሆነም ከአንብቦ መረዳትጋር በተያያዙ ሁለት ጥያቄዎችን ማንሳት እንደሚገባ Doll & others (1991) አያይዘው ይገልፃሉ፡ ከእነሱም አንደኛው ስለ አንብቦ መረዳት ምን ማስተማር ይገባል? የሚለው ነው፡ሁለተኛውም የአንብቦ መረዳት ትምህርት እንዴት መቅረብ አለበት? የሚለው ጥያቄ ነው፡

ስለአንብቦ መረዳት ምን ማስተማር ይገባል? ለሚለው ጥያቄ ምላሹ በአዕምሮአዊያን እይታ መሰረት አንብቦ መረዳትን አጋዥ የሆኑ ብልሀቶችን ማስተማር አለበት የሚል እንደሆነ O’mally and others(1990)፣ይጠቁማሉ፡ Armbruister and Bonnie (2002)፣ Heilman and Others(1998)፣ Notorn (1997)፣ ይህን ሀሳብ በማጠናከር ተማሪዎች ስለ አንብቦ መረዳት ብልሀቶች አስገንዝበዋል፡፡

ተማሪዎች በትምህርት አለም የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከሚያስፈልጓቸው ክህሎት አንዱ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ነው፡ ለምሳሌ - Hayland (1990)፣ Nelson (1984)፣ ከሌሎች ችሎታዎች ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ይከራከራሉ፡ በእርግጥም በትምህርት አለም የሚያልፉ ሰዎች በእየዕለቱ ከበርካታ ከሚነበቡ ነገሮች ጋር ስለሚገናኙ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በአግባቡ ካልጎለበተ ከፅሁፎች ተገቢውን እውቀት ይቀስማሉ ለማለት አይቻልም፡ ማንበብ ዘርፈ ብዙ ችሎታዎችን በተመሳሳይ ጊዜ ተግባራዊ ለማድረግ የአንድ ፅሁፍ መልዕክት መረዳትን ወይም መተርጎምን የሚጠይቅ ውስብስብ ክሂል በመሆኑ ክሂሉን ለማጎልበት መምህራን ለተማሪዎቻቸው ከክሂሉ ባሻገር የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ጭምር ማስተማር እንደሚጠበቅባቸው ያስገነዝባሉ፡

Aebersold and Field (1997)፣Haylabd (1990) ፣ Oxford (1990) ፣ wondon (1992) ፣ Willing (1989)፣ አንባቢዎች በቀደመ እውቀታቸው እና አዲስ በሚነበት ቴክስት ሀሳብ መካከል ትስስር መፍጠር የሚያስችላቸውን ብልሃቶች እስካልተጠቀሙት ድረስ አንብጦ አዲስ እውቀት ለማዋቀር እና ለሚዳት ሊያግዛቸው የሚችል ሚድ የማግኘት እድላቸው ዝቅተኛ ነው በማለት የአንብጦ ሚዳት ብልሃቶችን መማር ወሳኝነት ገልፀዋል፡፡ስለአንብጦ ሚዳት ተማሪዎች መማር ያለባቸው የአንብጦ ሚዳት ብልሃቶችን ጭምር ከሆነ ከላይ ወደቀረበው ወደ ሁለተኛው ጥያቄ ሲመጣ ትምህርቱ እንዴት መቅረብ አለበት የሚለው ይነሳል፡፡ የዚህ ጥያቄ ምላሽም ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን በመማር ዙሪያ ከሚሱ ጭብጦች ጋር በእጅጉ ይተሳሰራል O’Malley and Chamot (1990)፣ Wondon(1992)፡፡እነዚህን ብልሀቶች እንዴት ማስተማር ይቻላል? ከሚለው ጥያቄ ጋር ተያይዞ የሚሳ የመጀመሪያው ጭብጥም በተናጠል ወይም በውህደት ከመቅረባቸው ጋር ይያያዛል፡፡ ይህም በትምህርቱ ሂደት ብልሀቶቹ ብቻቸውን ተነጥለው ይቅረቡ ወይስ ከትምህርቱ ይዘቶች ጋር በውህደት ይቅረቡ የሚለውን ይመለከታል፡፡ በዚህ ሀሣብ ዙሪያ የሚሱ ክርክሮች መቋጫ ያላገኙ እንደሆኑ የሚጠቁሙት O’Malley and Chamot (1990)፣ ሁለቱም አቀራረቦች የየራሣቸው ጥንካሬና ደካማ እንዳላቸው አስገንዝበዋል፡፡ብልሀቶቹን ብቻ ነጥሎ መቅረቡ ተማሪዎቹ ሙሉ ትኩረታቸውን ብልሀቶችን በማካላት ላይ ብቻ እንዳያደርጉ ስለማያስችል በፍጥነት እንዲገነዘቡዋቸው ያስችላል የሚል ሙግት እንደሚቀርብበት Johonson and Others (1987)፣ በመጥቀስ O’Malley and Chamot (1990)፣ አመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጅ በብልሀቶቹ ላይ በተናጠል ማተኮር በሚቀርበው ትምህርት የሚገኘው የብልሀቶች እውቀት የትምህርቱን ይዘቶች በመማር ሂደት ላይ በተግባር የማዋሉ ጉዳይ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Collins and others (1990)፣ ብልሀቶችን ብቻ ነጥሎ ለማስተማር የሚያስችል የትምህርት አቀራረብ በብዙዎቹ ያንብጦ ሚዳት ማስተማሪያዎች ውስጥ ሲቀርብ እንደሚታይ ገልፀው በተናጠል መቅረቡ ጠቀሜታው ዝቅ ያለ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ከዚህ በተቃራኒ ብልሀቶቹን ከአንብጦ ሚዳት ይዘቶች ጋር በውህደት መቅረብ ተማሪዎቹ የብልሀቶቹን ተግባራዊነት የሚረዱበትንና የሚማሩበትን እድል ይፈጥራሉ፡እንዲሁም ተማሪዎቹ በአንዱ ይዘት አማካኝነት በተግባር የተማሩትን ብልሀት ወደ ሌሎች ተመሳሳይ ይዘቶችና ተግባራት በማሸጋገር ለመጠቀም እንዲችሉ በር ይከፍታል O’Malley and

Chamot፣ (1990)፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ አቀራረብ ተማሪዎቹን ከብልሀቶቹ ምንነትና ጠቀሜታ ጋር በግልጽ ማስተዋወቅ ይቻላል? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡እነዚህ ሁለት አቀራረቦች ያለባቸውን ችግሮች በማጣጣም ቢሆን በማስወገድ ሌላ የተለየ አማራጭን መጠቀም እንደሚቻል Deserdin(1985)፣ በመጥቀስ O’Malley and Chamot (1990)፣ ጠቁመዋል፡፡ ይህም አቀራረብ ተማሪዎች በአንድ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ወቅት ለአጭር ጊዜ ብልሀቶቹን ብቻ ነጥለው እንዲተዋወቁ ወይም እንዲማሩ ከተደረጉ በኋላ በማስከተል ከትምህርቱ ይዘት ጋር በማዋሀድ እንዲተገብሯቸው የሚያስችል ሁኔታን የሚፈጥር ነው፡

Armbruister and Bonnie (2002)፣ Heilman and Others (1998)፣ ደግሞ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን ወይስ በውህደት ማስተማር የሚለው ጭብጥ እያንዳንዱን ብልሀት ነጥሎ ማቅረብ ወይስ ብልሀቶቹን እንደአስፈላጊነቱ እያቀናጁ ማቅረብ ያስፈልጋል? ከሚለው ጥያቄ ጋር እንደሚተሳሰር ጠቁመዋል፡፡እያንዳንዱን ብልሀት እየነጠሉ ማቅረብ ተማሪዎቹ ብልሀቱን በስፋትና በጥልቀት እንዲፈትሹና እንዲገነዘቡት ያግዛል፡፡ብልሀቶቹ እንዳላቸው የአተገባበር ተመሳሳይነትና ተቃራኒነት እያቀናጁ ማቅረብ ደግሞ አንዱ ሌላውን የሚያጠናክርበትን እድል ስለሚፈጥር ተማሪዎቹ በተመሳሳይ ጊዜ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን እንዲጠቀሙ የሚያስችለ ግንዛቤ እንዲያገኙበት ይረዳል፡፡ አብዛኛው የአንብቦ መረዳት ሂደት በርካታ ብልሀቶችን በጥምረት መጠቀምን ከመጠየቁ አንፃር ብልሀቶችን በውህደት ማለማመዱ ተመራጭነት ያለው ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላው የአንብቦ መረዳት ብልሀቶቹን በመማር ዙሪያ የሚነሳው ጭብጥ ብልሀቶቹን በቀጥታ ወይስ በተዘዋዋሪ ማቅረብ ይገባል የሚለው ነው O’Malley and Chamot (1990)፣ Willig (1989)፡፡ የዚህ ጥያቄ ምላሽ እንደ ብልሀቱ ዓይነት፣ እንደ ተማሪዎቹ ልዩልዩ ሁኔታዎች የሚወሰን መሆኑንም Willig (1989)፣ አስገንዝበዋል፡፡ ብልሀቶቹን በተዘዋዋሪ ማቅረብ ይገባል የሚለው ሀሣብ አብዛኞቹ የትምህርቱ ተግባራት ተማሪዎች ለመማር የሚያስፈልጋቸውን ብልሀቶች ቀጥተኛ ባለሆነ መልኩ ለማስተዋወቅ ያስችላሉ፣ ከሚል ሃሣብ መነሻ የመነጨ ነው Willig (1989)፡፡ መምህራን እነዚህን ተግባራት ለተማሪዎቹ ሲያለማምዱ ምንም እንኳን ብልሃቶቹን ነጥለው ባያስተዋውቁም ብልሀቶቹን እያለማመዱ ጭምር እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ነገር ግን ለማስተማሪያ በሚቀርቡበት በብዙዎቹ ተግባራት ውስጥም ሆነ በማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ በተዘዋዋሪ ተካተው የሚገኙት የአንብቦ መረዳት

ብልሀቶች ካላቸው ጫልቀትና ውስብስብነት የተነሳ ላዘጋጅ ባለሞያዎች ሳይቀር በቀላሉ የሚታወቁ አይደሉም Willig (1989)፡፡ በሙሆኑም ተማሪዎቹ ብልሀቶቹን ተገንዝበው ይተገብሯቸው ዘንድ መማር እንደሚያስፈልጋቸው Wondon (1991)፣ ያስገነዝባሉ፡ ይህም ተማሪዎቹ ስለአንብቦ ሚዳት ብልሀቶቹ ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ አተገባበር ግልጽ ማብራሪያ እየቀረበላቸው በቀጥታ የሚማሙበትን አቀራረብ መጠቀም ይጠይቃል O'Malley and Chamot (1990)፡፡

የቋንቋ መማር ብልሀቶችን በግልጽ ለማስተማር የተለያዩ ፀሀፍት የየራሳቸው የአቀራረብ ቅደምተከተል ንደፍ /frame work/ ሲያቀርቡ ይስተዋላሉ፡ Heilman and Others (1998)፣ Wondon (1992)፣ እንደጠቆሙት ብልሀቶቹን በቀጥተኛ መንገድ ለማስተማር አንዱ የአቀራረብ ቅደምተከተል ለትምህርቱ የሚቀርበውን ብልሀት በማሳየት፣ ሞዴል በማድረግ

ማለማመድ፣ ድጋፍ በመስጠት ማለማመድ፣ ሂደቱን ማማማም ወይም ጽብረቃ ማድረግ በመጨረሻም ልምምድ የሚያደርጉባቸው ተግባራትን ማቅረብ የሚሉትን ደረጃዎች ማለፍን ይጠይቃል፡፡ Williyams and Berden (1997)፣ O'Malley and Chamot (1990)፡ የተለያዩ ጸሀፍት በተግባር ላይ ያዋሉዋቸውን የተለያዩ የብልሀት ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተሎችን አስፍረዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ቋንቋን ጨምሮ ለሌሎች ትምህርቶችም ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚችል የተገለጸው Johonson and Others (1981)፣ በማቀስ O'Malley and Chamot (1990)፣የአንብቦ ሚዳት ብለሀቶችን ለማቅረብ ተግባራዊ የተደረገው ቀጥተኛ የብልሀቶች ትምህርት አቀራረብ ቅደምተከተለ ይገኝበታ፡ እነዚህ ጸሀፍት ያሰፈሩት የአንብቦ ሚዳት ብልሀቶች አቀራረብ ቅደምተከተልም ተጠቃሎ ሲታይ የሚከተለውን ይምስላል፡፡

## ሀ. ዳራዊ ፍተሻ ማካሄድ

ይህ የመማር ብልሀቶችን በማስተማር ሂደት በቅድሚያ መከናወን ያለበት ተግባር ነው፡ ተማሪዎቹ በጊዜው እየተጠቀሙባቸው ያሉትን የመማር ብለሀቶች ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ክንዋኔዎችን የሚተገብሩበት ነው፡ በተለይም ለማስተማር የሚፈለገውን ብልሀት በሚመለከት ተማሪዎቹ ያላቸው ዳራዊ ግንዛቤ ለማግኘት የሚያስችል ስራ የሚሰራበት ነው፡

በዚህ ደረጃ የሚፈጸሙ ክዋኔዎችን በብልሀቶቹ አጠቃቀም ዙሪያ ተማሪዎች ያላቸውን ልምድ ማጣየቅ ወይም በቃል ማጠይቅ ለሚፈተሽ ማጣቅር ወይንም በማምህሩ ምሪት ተማሪዎች ቀደም ብለው ስለ ብልሀቶቹ በሚያውቁት ሀሣብ ዙሪያ እንዲወያዩ ማድረግ ወይም የብልሀቱቹን አጠቃቀም በሚማለከት ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ ቅደመ ስልጠና ማስጠት ናቸው፡ በጥቅሉ ይህ ደረጃ ተማሪዎች አዲስ የሚቀርብላቸውን የመማር ብልሀት ከማተዋወቃቸው በፊት ቀደም ብሎ በትክክልም ይሁን በተዛባ አቅጣጫ ከብልሀቱ አጠቃቀም ጋር ያላቸውን ትውውቅ ለማንዘብ ያስችላል፡፡ ይህ ግንዛቤም በቀጣይ የሚተገበሩትን የብልሀቱን ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች በአግባቡ ለማቅወን ማሰረት የሚኗል ይሆናል፡፡

## ለ. ታላሚውን ብልሀት ማስተዋወቅ

ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚጠቀሙባቸው የመማር ብልሀቶች ከተለዩ በኋላ አዲስ ለመማር ከተዘጋጀላቸው ብልሀት ጋር እንዲተዋወቁ ይደረጋል፡፡ በዚህ ደረጃ አዲስ ከሚቀርብላቸው የመማር ብልሀት ጋር በስም ማስተዋወቅ፣ የብልሀቱን ጥቅሞች በግልጽ ማነገር፣ ብልሀቱን የማጠቀም ምክንያቶችን ማገለጽ፣ ብልሀቱን እንዴት ሊተገብሩት እንደሚችሉ ደረጃ በደረጃ

ማገለጽና ብልሀቱን በምን ዓይነት አውድ ውስጥ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ማስረዳት ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ይህ ሂደት ተማሪዎቹ እንዲማሩት ከተፈለገው የመማር ብልሀት አጠቃላይ ገጽታዎች ጋር የሚተዋወቁበትና ብልሀቱን ለማተግበር ወይም ለማለማመድ የሚዘጋጁበት ነው፡

## ሐ. በምሪት ማለማመድ

ይህ ደረጃ ማምህሩ ለተማሪዎቹ ያስተዋወቀው የመማር ብልሀት እንዴት በተግባር እንደሚውል እየሰራ የሚያሳይበት ብሎም ተማሪዎቹ ከማምህሩ የቀረበላቸውን ተግባራዊ ትውውቅ ማሰረት አድርገው የብልሀቱን አተገባበር የሚለማመዱበት ነው፡ ማምህሩ የብልሀቱን አተገባበር ለተማሪዎች ለማስተዋወቅም ምሪትን ይጠቀማል፡፡ ይህም የብልሀቱ አጠቃቀም በማምህሩ እየተተገበረ ተማሪዎቹ የአተገባበሩን ሂደት የሚከታተሉበት ነው፡ እንደ Heilman and others (1998)፣ አገላለጽ ማምህሩ የሚያከናውነው የምሪት ተግባር ሁለት ገጽታዎች አሉት፡ "ቶክ አላውድ" ምሪት የመጀመሪያው ሲሆን ማምህሩ አንድ

የአንብቦ መረዳት ብልሀት የሚጸሟቸውን ደረጃዎች በተግባር ሲያሳይ ተማሪዎቹ በመሀል ስለብልሀቱ አፈጻጸም ልዩ ልዩ ጥያቄወችን እያነሱ ለእያንዳንዱ ተግባር ሚፀም ምክንያቶችን እንዲገነዘቡ የሚያደርግበት ነው፡ ሁለተኛው ደግሞ እሣቤን ማሰማት /ቲንክ አላውድ/ ምሮት ሲሆን ብለሀቱ የሚጸምባቸውን ደረጃወች መምህሩ ከማንገር ባለፈ ተግባሮችን ሲያከናውን ምን ዓይነት አዕምሮአዊ ሂደትን እያከናወነ እንደሆነ ለተማሪዎቹ የሚያስተዋውቅበት ነው፡ በመሆኑም ተማሪወቹም ከብልሀቱ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ምን ዓይነት አእምሮአዊ ሂደት እንደሚከናወን መምህሩን ጠይቀው በሚረዳት እነሱም በተመሳሳይ በተግባራት ላይ እንዴት ይህንን ሂደት እንደሚገብሩት የሚረዱበት ነው Heilman and others (1998)፡፡

**መ. በድጋፍ ማለማመድ**

ተማሪዎቹ ስለአንድ የአንብቦ መረዳት ብልሀት ማለትም ስለማጠቃለል/ summarizing / ምንነትና ጠቀሜታ ከተገለፀላቸው በኋላ መምህሩ በሚያደርግላቸው ምሮት ከተለማመዱ በኋላ ብልሀቱን በተግባር እየተጠቀሙ የሚያሳዩበትና የሚለማመዱበት ክዋኔ ይቀርብላቸዋል፡፡ በዚህ ደረጃም ተማሪወቹ በግል ከሚያደርጉት ልምምድ በተጨማሪ በጥንድና በቡድን አተገባበር በጋራ እንዲለማመዱ ይደረጋል፡፡ በሂደቱም መምህሩ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል የተዋወቁትን ብልሀት ምን ያህል በአግባቡ እየተገበሩት እንደሆነ ክትትል ያደርጋል፡፡ በክትትሉም ተማሪዎቹ ከብልሀቱ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ያጋጠሟቸውን ችግሮች እንዲፈቱ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የሚሰጠው ድጋፍም በመጀመሪያ ሰፋ ያለ ሆኖ ቀስ በቀስ እየቀነሰ የተማሪዎቹን

ራሣቸውን ችለው ብልሀቶቹን የሚገብሩበት ሁኔታ በመፍጠር ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

**ሠ. ግምገማ ጽብረቃ**

ይህ ደረጃ ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ብልሀት በመተግበር በብቃታቸው ዙሪያ ራሣቸውን የሚመገሙበት ነው፡ ይህም ተማሪዎቹ ብለሀቱን በመጠቀም ሂደት ያጋጠሟቸውን ችግሮችና ችግሮቹን የፈቱበት ስልት የሚለጹበት፣ ስለብልሀቱ ጥቅም በጋራ ውይይት የሚያደርጉበት፣ ከብልሀቱ አተገባበር ጋራ በተያያዙ

የግንዛቤ ማጣከሪያ ጥያቄወች ምላሽ የሚሰጡበት፣ ብልሀቱን በማግበር በኩል የተሰማቸውን ስሜት የሚገልጹበት፣ ብልሀቱን እንዴትና በምን ሁኔታ አጠናክረው ማግበር እንደሚችሉ የሚያስረዱበት ነው፡

**ረ. ተጨማሪ ልምምድ ማድረግ**

ቀደም ብሎ በተማሩት መሰረት ተመሳሳይ ተግባራት ቀርበውላቸው ብልሀቶቹን የሚለማመዱበት ደረጃ ነው፡ ይህ ደረጃ በዋናነት ተማሪዎቹ ብልሀቶቹን ራሳቸውን ችለው ማግበራቸውን የማጠናከር ዓላማ ያለው ነው፡ እንዲሁም ብልሀቶቹን በአዳዲስ ተግባራት ላይ ምን ያህል እንደሚገብሯቸው በራሳቸው ለማማም ጥራ የሚያደርጉበት ደረጃ ነው፡ ከዚህም ሌላ ተማሪዎቹ ምን ያህል የተማሩትን ብልሀት በግላቸው አጠናክረው እየተገበሩት እንደሆነና የብልሀቱን ትግበራ ቀጣይነት ለማማም ይረዳቸዋል፡፡

## 2.5. የአንብቦ መረዳት ብልሀት ዓይነቶች

የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች በቁጥር እጅግ በርካታ ናቸው፡ ቋንቋ የመማር ብልሀቶችን በስፋት ተንትነው ያቀረበት Oxford(1990)፣ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በማስተማር ዙሪያ በተሰሩ ጥናቶች ፍተሻ ያደረጉት በርካታ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን ለይተው አስፍረዋል፡፡

"National Reading penel"(2002)ን፣ በመጥቀስ Armbruster and Aseborn (2002)፣ እንዳስረዱት ደግሞ ፖናሉ ያወጣቸውን መስፈርቶች ካሟላት ውስጥ መመስጠር ፣ ዋና ሃሣቡን ማለየት፣ ማጠቃለል፣ ምስል ፈጠራ፣ ጥያቄ መጠየቅ ወይም ማመንጨት ፣ ጥያቄ መመለስ ፣የሚሏት ይገኙበታል ፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ግኝኑነት ያለውን የማጠቃለል ብልሀትን ለማየት ይሞከራል

**ማጠቃለል / summarizing /፡-** አንድ በዝርዝረ ተለጥጦ የቀረበ ጽሁፍ በማጎበበ ሃሣቡን በታማኙና በተመጠነ መልኩ ለማስፈር የሚያስችለ የአንብቦ መረዳት ብልሀት ማጠቃለል ይባላል Oxford(1990)፡፡ የጽሁፍን ዋና ዋና ሀሣቦች ለይቶ ማውጣትን የሚጠይቀው ይህ ብልሀት የመጣሻ ጽሁፍን ይዘት እንዳለ በመጠበቅ በቅርጹ ላይ ሰፊ ማሻሻያ ማድረግንም ይፈልጋል፡፡

ማጠቃለል ለአንድ ጽሁፍ ጠቃሚ ሀሣቦችን ከማለየት ባሻገር ሃሣቦችን በተገጣጠመ በሰመረ መልኩ የመጻፍ ችሎታን የሚጠይቅ እንደሆነ Notorn (1997)፣ ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጅ Head and

Andorson (1986) በመጥቀስ Doll and others (1991)፣ ማጠቃለልን ጸሀፊ- ተኮርና አንባቢ-ተኮር በሚል መክፈል የሚቻል መሆኑን ጠቁመው ተማሪዎች ጸሀፊ-ተኮር ማጠቃለልን እንዲለማመዱ በማድረግ ከመጻፍ ችሎታ ይልቅ በአንበቦ መረዳት ችሎታ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ እንደሚቻል አስገንዝበዋል፡፡

እንደ Doll and others (1991)፣ ሀሣብ ጸሀፊ-ተኮር ማጠቃለያ ዋናውን ጽሁፍ እያነበበ ማጠቃለያውን በሚጽፈው ሰው የሚነበብ በመሆኑ ለአደረጃጀትና ለጽህፈት ብዙም ትኩረት ሣይሰጥ ሊከወን የሚችል ነው፡ በመሆኑም የአንባቢው ትኩረት የጽሁፍን መልእክት በመረዳት ላይ እንዲሆን እድል ይሰጣል፡፡

ይሁንና ብዙዎቹ ከማጠቃለል ብልሀት ጋር ተያያዘው ለተማሪዎቹ የሚሰጡ የአንበቦ መረዳት ተግባራት አንባቢ ተኮር ማጠቃለያ ላይ እንዲያተኩሩ የሚያበረታቱ እንደሆኑ Doll and others (1991)፣ ያመለክታሉ፡፡ ይህ የማጠቃለያ አቀራረብ ስልት ተማሪዎቹ ማጠቃለያውን ለሌላ አንባቢ በማቅረብ መልኩ እንዲያዘጋጁ ስለሚጠበቅ ለጽሁፍ እርዝመት፣ ለሰዋሰው አወቃቀሩና ስለግጥምጥምነቱ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ተግባራት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ብልሀት የሆነውን ማጠቃለልን ከመረዳት ብልሀት ወደ መጻፍ ተግባርነቱ እንዲያመዝን የሚያደርጉት ይሆናሉ፡፡

ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ጠቃሚ ዝርዝር ሃሣቦችን ጨምቆ ማውጣትን እንደሚጠይቅ የሚያገናዝቡ Armbruister and Andobsorn (2002)፣ ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀትን ለማለማመድ በርካታ ቴክኒኮችን መጠቀም እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡ የመጀመሪያው ቴክኒክም የአንድን ቴክስት መዋቅር መሰረት ያደረጉ ቁልፍና የአጠቃላይነት ሀሣቦን የሚያመለክቱ ቃላትንና ሀረጋትን በማሥፈር ተማሪዎቹ ጽሁፍን እያነበቡ በሚሆ ቃላቱና ሀረጋቱ ሥር

የሚቷተቱ ሀሳቦችን እየለዩ እንዲያሰፍሩ በማድረግ የሚከናወን ነው፡ ለዚህም መምህሩ የሚያቀርባቸውን መሪ ሀሳቦች ተማሪዎቹ ጽሁፉን ሲያነቡ የትኛው ክፍል ላይ ማተኮር እንዳለባቸው የሚጠቁሙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ሌላው የማጠቃለል ብልሀትን ለማለማመድ የሚያስችል ቴክኒክ እርከናዊ አጠቃሎ/ Hierarchical summary/ Tayler and Bich (1984)፣ Taler and Berkiyutis (1980)፣ በመጥቀስ Armbruister and Andobsorn(2002)፣ ያስረዳሉ፡ ይህን ቴክኒክም ለመተግበር በማሻ ላይ ተማሪዎቹ ጽሁፍን እያነበቡ ርእሶቹን፣ ንኡስ ርዕሶቹን እና አንቀጾቹን መሰረት አድርገው ንድፍ ያዘጋጃሉ፡በመቀጠልም በየርእሶቹ፣ በየንኡስ ርእሶቹና በየአንቀጾቹ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሀሣቦችን ለይተው ያወጣሉ፡ በመጨረሻም በየደረጃው ያወጧቸውን ዋና ዋና ሀሳቦች መሰረት በማድረግ አንድ መሪ ሀሣቡን በመፍለቅና ዋና ዋና ሀሳቦችን በመሪው ሀሣብ ስር በማስተሳሰር የምንባቡን ጠቅላላ ሀሣብ ይገልፃሉ፡

የማጠቃለል ብልሀትን መሰረት በማድረግ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ሌላው አማራጭ ስልት በተለያዩ ተመራማሪዎች የተፈተሸና የዳበሩ የማጠቃለያ አቀራረብ ህጎችን መጠቀም እንደሆነ Birawen and Diay(1983)ን፣ እንዲሁም Riharit,Stahal,Arixen(1986)ን፣ ዋቢ በማድረግ Armbruister and Andobsorn (2002)፣ ያስገነዝባሉ፡ እነዚህም ህጎች አላስፈላጊ መረጃዎችን ከሚበበው ጽሁፍ ውስጥ መሰረዝ፣ የተደጋገሙ መረጃዎች ካሉ መሰረዝ፣ ክፍፍልን የሚያሳዩ አገላለፆችን አጠቃላይነት ባላቸው ቃላትና ሀረጋትን በመጠቀም ማጠቃለል፣ በጽሁፍ ውስጥ የተገለጹ ሀይለቃሎች ወይም ዋና ሃሣቦች ካሉ እንደመሪ ሀሣብ አድርጎ መጠቀም፣ ጸሀፊው የየአንቀጹን ዋና ሀሣብ በኃይለቃል መልኩ ያላሰፈረ ከሆነ በአንባቢው በኩል የራስን ሀይለቃል መፍጠር ናቸው፡

## 2.6. ማጠቃለል አንብቦ መረዳት ብልሀትን በመማር ሂደት የተማሪዎች ባህሪያት ያላቸው ተጽዕኖ

የተማሪዎች ልዩ ልዩ ባህሪያት የመማር ብልሀቱን በሚያስከት የሚቀርበውን ትምህርት ስኬታማ ለማድረግም ሆነ በማደናቀፍ በኩል ከፍተኛ ሚና አላቸው፡ የተማሪዎቹ የቋንቋ ብቃት ደረጃ ፣ የማቃቃት ሁኔታቸው፣

ያታቸው፡ቀደምት የትምህርት ደረጃቸው፣ የመማር ስልቶች ምርጫዎቻቸው በብልሀቶች ስልጠና ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳደሩ ባህሪያት ጥቂቶቹ ናቸው፡ Hilima (1998)፣ O'Malley & Chamot (1990)፣ Wondon (1992)፣ Williams & Burden (1997)፡፡

የቋንቋ ብቃት ደረጃቸውን በሚመለከት የብልሀት ትምህርቱ በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ የሚቀርብ ከሆነ በጀማሪ የትምህርት ደረጃ እያሉ ጀምሮ ሊቀርብላቸው በአግባቡ ሊከታተሉት ይችላሉ፡በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ ግን የአንብቦ መረዳት ብላሀቶቹን ጨምሮ አብዛኞቹን ብልሀቶች ለመቅረብ የተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት የተሻለ ደረጃ ላይ እስከሚደርስ መጠበቅ አስፈላጊ ነው የሚል ሀሣብ ይሰነዘራል O'Malley & Chamot (1990)፡፡ ይሆን እንጅ Wondon (1987)፣ጋር ያደረጉትን ግለሰባዊ የሃሣብ ልውውጥ በመጥቀስ O'Malley & Chamot (1990)፣ አያይዘው እንዳብራሩት ከሜታኮግኒቲቭ ስልቶች ጋር የተያያዙ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ለተማሪዎቹ ቀድመው በማስተዋወቅ ትምህርቱን መስጠት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል አንዳንዶቹን የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ለሚገኙት በቋንቋው የዳበረ እውቀት ለሌላቸው ተማሪዎች መቅረብ አስቸጋሪ እንደሆነ የሚጠቁሙ ጽሁፍት አሉ፤ ለአብነትም Berih and Berchanden (1984) Tayler and BIch (1984)ን፣ በመጥቀስ Dole and others (1991)፣ እንደጠቆሙት የማጠቃለል ብልሀት መካከለኛና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች መቅረብ ያለበት ነው፡ ከስደስተኛ ክፍል በታች ያሉ ብዙዎቹ ተማሪዎች ቁልፍ የሆኑና ያልሆኑ ሀሣቦችን አንብበው በመለየት በኩል ችግር ስለሚጋጥማቸው የማጠቃለያ አያያዝ ብልሃትን ማስተማር አስቸጋሪ እንደሆ አመላክተዋል፡፡ ብልሀቶችን በማስተማር ሂደት ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ሌላው ነጥብ የተማሪዎች ፍላጎት ሁኔታ ነው፡ ብልሀቶቹን በማስተማር ሂደቱ በማጎልበት ላይ ተማሪዎች ጥሩ የመነ ቃቃት ሁኔታ ላይታይባቸው ይችላል Wondon (1992)፡፡ በመሆኑም Paris (1988)ን፣ ዋቢ በማድረግ O'Malley and Chamot (1990)፣ እንዳሰፈሩት በብልሀቶች ትምህርት ውስጥ ምሪትን ቀጥተኛ ገለፃን፣ በድጋፍ ማስተማርንና ተማሪዎቹ በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ በመፍጠር መነ ቃቃትን መፍጠር ይጠበቃል፡፡ በዚህ ሂደትም ተማሪዎቹ ከዕለት ወደ ዕለት የሚያመጡትን የመነ ቃቃትና የግንዛቤ

ለውጥ መፈተሽ ተገቢ ይሆናል፡፡ ያመጡትን ለውጥም ለመፈተሽ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የጽሁፍ መጠይቅንና የማጣቀሻ ቅጽን በመጠቀም መረጃ መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ Wondon (1992)፣ Brown (1994)፣ Williams and Burden (1997) አስገንዝበዋል፡፡ ብልሀቶችን በመማር ሂደት ሊተኮርበት የሚገባው ሌላው የተማሪዎች

ባህሪ የመማር ስልት ምርጫዎቻቸው ልዩነት ነው፡ Willing (1989) በማስተማር ሂደት የተማሪዎችን የመማር ስልቶች ምርጫ ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ የተለያዩ የመማር ስልቶች ምርጫዎች ያላቸውን ተማሪዎች ለተለያዩ የመማር ብልሀቶች አቀራረብ የሚሰጡት ምላሽም ተመሳሳይ አይሆንም፡ ለምሳሌ ያህል ጀማሪ ለሆኑ ፣ ከፍተኛ አውድ ጥገኝነት /Field dependent/ ለሚታይባቸው በተናጠል መስራት ለማይመርጡ ነገሮችን ለመተንተን ምርጫ ያላቸው ብልሀቶችን እየዘረዘሩ በቀጥታ ማቅረብን ወይም መማርን አይመርጡም፡ ለተማሪዎች የመማር ስልቶችና የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ትምህርት አቀራረብ ምርጫዎቻቸው መካከልም ዝምድና እንዳለ በጥናቶች ለመፈተሽ ሙከራ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተቃራኒው ተማሪዎችን እንደ መማር ስልቶች ምርጫዎቻቸው ማስተማር ከውጤታቸው መሻሻል ጋር ግንኙነት እንደሌለው የሚያመለክቱ ጥናቶች አሉ፡ ለምሳሌም Muler (1992), ዋቢ ያደረጋቸው Kronbah and VOnow (1977)፣ Campwreze and Batas (1980)፣ Temadan (1999)፣ ባደረጓቸው ጥናቶች ተማሪዎችን እንደመማር ስልት ምርጫዎቻቸው ማስተማር ውጤታቸውን ያሻሽላል የሚለውን አስተሳሰብ የሚቃረን ውጤት ማግኘታቸው ተጠቁሟል፡፡ እንዲሁም Clark (1982)፣ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ተማሪዎች በሚመርጡት የማስተማር ዘዴና በውጤታቸው መካከል ተዛምዶ እንደሌለ Muller (1992)፣ አመልክተዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የተገለፀው አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ ከሚመርጡት የመማር ስልት የበለጠ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይንም ሊማሩ መቻላቸው ነው፡ ከዚህ አንፃር የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን በቀጥታ መማር ከተማሪዎች የተለያዩ የመማር ስልቶች ምርጫዎች ዝምድና ያለው ወይም የሌለው መሆኑን በጥናት ለመፈተሽ የተሻለ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

## 2.7. የቀደምት ጥናት ቅኝት

ስለማንበብ ክሂል የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በሀገር ዉስጥ የተሰሩ ጥናቶች በአብዛኛው በአንብቦ ሚዳት ላይና ለአንብቦ ሚዳት የሚጠቅሙ ግብዓቶች ማለትም የፅሁፍ ቅንጫቢዎችና ልቦለዶችን በመጠቀም እንዲሁም ለአንብቦ ሚዳት ትብብራዊ መማር ዘዴ ያላቸዉን አስተዋፅ የሚያሳዩ ጉዳዩችን አጥኝው ባደረገው ዳሰሳ ለማየት ችሏል፡፡ በመሆኑም አንዳንዶቹን ለማየት ይሞክራል፡፡

የመጀመሪያው የታምሩ ፣ (2008)፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስትሪት ዲግሪ ማሟያነት የቀርበ ጥናት ነው፡ ጥናቱ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከቀርበ ጥናት ሲሆን "በበርትኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ ሚዳት ችሎታ ጾታ ተኮር ጥናት" በሚል ርዕስ ያካሄደው ነው፡

የጥናቱ ዓላማዎች በበርትኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ወንድና ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የሚዳት ችሎታ ልዩነት መመርመርና በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል አንብቦ የሚዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ለመሆኑ ምክንያቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ሚፈተሽ ነው፡

ይህንን ዓላማ ለማካካት ምርምሩ በመጠናዊ ዘዴ ሚጃዎችን በተለያዩ የሚጃ መሰብሰቢያ አይነቶች አማካኝነት በማሰብሰብ የመተንተንና የመተርጎም ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህ መሠረት በጥናቱ የተደረሰበት ድምዳሜ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ በበርተኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የሚዳት ችሎታ በቂ መሆኑንና በወንድና በሴት

ተማሪዎች መካከል አንብቦ የሚዳት ችሎታ ልዩነት አለመኖሩን የደረሰባቸው ሚደምደሚያ ናቸው፡ ይህ የተደረገ ጥናት ከታምሩ፣ (2008)፣ ስራ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ችሎታን ሚፈተሽ ሲሆን ጥናቶችን የተለያዩ የሚያደርጋቸው የታምሩ ጥናት በአማርኛ ኢ- አፈ ፈት በሆኑ ተማሪዎች እና ፆታ ተኮር ጥናት ሲሆን ይህ ጥናት የሚያተኩረው የተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ ሚዳት ችሎታ ላይ በመሆኑ እና በአማርኛ አፈ-ፈት በሆኑ

ተማሪዎች የሚሰሩ መሆኑ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የታማኙ የመረጃ መሰብሰቢያ በመጠናዊ ዘዴ ሲሆን ይህ ጥናት የሚጠቀመው ግን በመጠናዊና አይነታዊ (ቅልቅል) ዘዴ በመሆኑ ይለያል፡፡

ሁለተኛው ደረጃ የከድር ፣ (2009)፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሂዩሚቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስትሪት ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ ከመሃ ትምህርት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ በሚል በያዩ አይዳቲያ እና የጣሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት ነው፡

የጥናቱ ዓላማዎች ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከመሃ ትምህርቱ ላይ ከተቀመጠው አጥጋቢ መሟ ማስተማሪ ብቃት ሚጋገጫ (MLC) ላይ መድረስ አለመድረሱን ሚፈተሽ ሲሆን መረጃዎች የሰበሰሰበባቸው በመጠናዊና አይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን ለተማሪዎች የንባብ ችሎታ ማእከያ ፈተና እና ለመምህራን በቃለ መጠይቅ ነው፡ የጥናቱ ውጤት የሚያመለክተውም በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች በተሰጣቸው አንብቦ መረዳት ፈተናዎች በጣም ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገብ፤ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከመሃ ትምህርቱ ከተቀመጠው የችሎታ ብቃት ሚጋገጫ (MLC) ላይ እንዳልደረሰ አሚልክቷል፡፡

ይህ ጥናት ከከድር ፣ (2009)፣ ስራ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ መሆኑ ይሆናል፡፡ እነዚህን ጥናቶች የተለያየ የሚያደርጋቸው የከድር ጥናት አንብቦ መረዳት ችሎታ ከመሃ ትምህርት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ የሚፈትሽ ሲሆን ይህ ጥናት የሚተከረው የተማሪዎችን የማንቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ የሚፈትሽ በመሆኑ ነው፡

በመጨረሻም የመሪነሽ፣ (2004)፣ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩሚቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስትሪት ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ በጎንደር ከተማ የእድገት

ፈለግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች "የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ" በሚል ርዕሰ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡ የጥናቱ ዓላማ በማንበብ ተነሳሽነት እና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ሲሆን በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመችባቸው

መሳሪያዎች ፈተናና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡ የጥናቱ ውጤት የሚያመለክተውም በጾታና በማንበብ ተነሳሽነት መካከል፣ በፆታዊና በውስጣዊ የንባብ ተነሳሽነት መካከል፣ በፆታና በአንብቦ መረዳት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን እና ነገር ግን በጾታና በውጫዊ የማንበብ ተነሳሽነት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን በዚህም ሴት ተማሪዎች በአንፃሩ ከወንድ ተማሪዎች ጉልህ ብልጫ ያላቸው መሆኑን በጥናቷ አመልክታለች፡፡

ይህ ጥናት ከሚኒሽ፣ (2004)፣ ስራ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ በማንበብ ክሂል ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውና የተመሰረተ መሆኑ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ የሚኒሽ ጥናት የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት የሚያተኩረው የተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ ማየተሸ መሆኑ ነው፡

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው አጥኚው በዳሰሳ እንደሚያመለከተው በሀገር ውስጥ የተጠኑት ጥናቶች ለአንብቦ መረዳት የተለያዩ ግብዓቶች ያላቸውን ሚና የሚያሳይ ሲሆን የተዳሰሱት ጥናቶች ለአንብቦ መረዳት ያላቸውን መዳሰስ ብቻ ነው፡ በመሆኑም አንብቦ ለመረዳት የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳላቸው የዚህ ጥናት አጥኚ ያምናል፡፡ በመሆኑም ሌሎች ይህንን ብልሀት የዳሰሱበት ሁኔታ ስለሌለ ክፍተት ነው ብሎ በማመን ይህንን ክፍተት ለማየት የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች ከሆኑት መካከል የማጠቃለል ብልህትን ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ ለመዳሰስ ተነሳስቷል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ዓላማ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ የመማሪያ መጽሐፍ ተግባራትን ውጤታማነት መፈተሽ ነው፡ ይህ ጥናት የተከተለው የአጠናን ዓይነት መጠናዊ እና አይነታዊ የአጠናን ዓይነት ሲሆን የሚከተለው የጥናት ንድፍ ደግሞ ከፊል መከራዊ በመሆኑ የሁለት ቡድኖች ማለትም የቁጥጥር ቡድን እና የመከራ ቡድን የቅድመና ድህረ ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ሁለቱ ተጠኚ ቡድኖች ምንም ሳይማሩና ከተማሩ በኋላ ባስመዘገቧቸው የፈተና ውጤቶች አማካይነት ያሳዩትን የማዳመጥ ክሂል ልዩነት መርምሯል፡፡

### 3.2. የናሙና አመራረጥ

#### 3.2.1. የትምርት ቤት አመራረጥ

ለዚህ ጥናት አካባቢ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በእነማይ ወረዳ ከሚገኙ ሶስት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በብቸና ከተማ የሚገኘው የበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የአጥኚው የመኖሪያ አካባቢ እና የስራ ቦታ በመሆኑ ለጥናቱ መካካት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር፣ መምህራን እና ተማሪዎች ድጋፍ እና ትብብር ማግኘት ይቻላል በሚል ታሳቢ ለጥናቱ ማካናዎኛነት አመቺ የናሙና ዘዴ በመጠቀም ተመርጧል፡፡

#### 3.2.2. የተማሪዎች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጡት ተማሪዎች በብቸና በላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ የተመረጡበት ምክንያትም አጥኚው ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ባሰበበት ጊዜ በትምህርት ላይ ስለሚገኙ በቂ ጊዜ እንዲኖረው ስለሚያስችል ነው፡ ከዚህ ባሻግር ዘጠነኛ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚጀምሩበት በመሆኑ ችግሮች ካሉ ከስሩ ጀምሮ ለመፍታት ጥረት በማድረግ

ለቀጣዩቹ የክፍል ደረጃዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ ነው፡ ዘጠነኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል በመሞከር ማስተማሩ ሂደት ዘጠነኛ ክፍል ከሚያስተምሩ አራት መምህራን መካከል በቀላል የእጣ ሰጭ ዘዴ አንድ መምህር በማምረጥ መምህሩ ከሚያስተምሯቸው አራት ክፍሎች ውስጥ በሎተሪ መንገድ ሁለቱን ክፍሎች በማምረጥ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ እነዚህም የሚመረጡቱ የእጣ ሰጭ የናሙና ዘዴ በተለይም በሎተሪ የናሙና ዘዴ ነው፡ በመሆኑም በአንድ መምህር ከሚማሩ ክፍሎች መካከል በሎተሪ የናሙና ዘዴ ሁለት ክፍሎች ተመርጠው በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በመሆኑም አጥኚው በተጠኝነት የተመረጡትን ክፍሎች ውስጥ ያሉትን ዘጠነኛ E (58 ተማሪዎች ወንድ 31፣ ሴት 27) የሙከራ ቡድንና ዘጠነኛG (60 ተማሪዎችን ወንድ 29፣ ሴት 31) ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ይዞ ለማስተማር ክፍለ ጊዜ በማዝ ተግባራዊ አደርጓል፡፡ ይህም የመሞከር ማስተማሩ ክዋኔ የሚካገበረው ከሚያዚያ 15 2011 ዓ.ም እስከ ግንቦት 15/ 2011 ዓ.ም ድረስ 8 ክፍለ ጊዜ በሳምንት ለሁለት ክፍለጊዜያት ያክል ከሚደበኛው የመሞከር ማስተማር ክፍለጊዜ በተቃራኒ ፈረቃ የትምህርት ቤቱን አስተዳደር ፈቃድ በመጠየቅ እና ፈቃድ በማግኘት ተማሪዎች ለጥናት እንደሚፈለጉ ተነግሯቸው እና በቃደኝነታቸው ተጠይቀው ፈቃደኛ በመሆናቸው ሁለቱም ክፍሎች እያንዳንዳቸው በቀን ለ40 ደቂቃ በማስተማር ሲሆን የሙከራ ቡድኑን የማጭቃለል ብልሀትን ብቻ በማስተማር ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ መደበኛውን የመሞከር ማስተማር ሂደት በመከተል ለተማሪው የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፅሀፍ በመጠቀም ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 3.2.3 የጥናቱ አካባይ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በእነማይ ወረዳ የሚገኙ ሶስት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ፡ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በብቸና ከተማ የሚገኘውን የበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን የጥናቱ ተሳታፊዎች በዚህ ትምህርት ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል 915 ተማሪዎች ውስጥ ከአሰራ ስደስት ክፍሎች ውስጥ የሁለት ክፍል ተማሪዎች እና በዚህ የክፍል ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው፡

## 3.3 የመረጃ ማሰብሰቢያ ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሁለት መሳሪያዎችን አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ይህም አንብቦ የሚገኑት ፈተናና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡

### 3.3.1 ፈተና

የአንብቦ መረዳት ፈተና የዚህ ጥናት አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ነው፡ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት እና የማጠቃለል ብልሃት ውጤቱን መረጃ ለማግኘት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የአንብቦ መረዳት እና የማጠቃለል ብልሃት ፈተናው ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኖች ቅድመ ትምህርት ፈተናና ድህረ ትምህርት ፈተና መስጠትና ውጤቶችን መመዝገብ፣ እንዲሁም በተጠኝነት የተያዙት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ከመማራቸው በፊት ያለውንና ከተማሩ በኋላ ያላቸውን የምንባብ ክሂል የማጠቃለል ብልሀትን ማየት ነው፡

በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎች አንድ ፈተና በቅድመ ትምህርትና አንድ ፈተና በድህረ ትምህርት እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ፈተናው የክፍል ደረጃውን መሰረት አድርጎ በአጥኚው ተዘጋጅቷል፡፡

የተዘጋጀውም ፈተና የምንባብ ክህሎትን ይሄውም የማጠቃለል ብልሀትን ለሚፈተሸ የሚያገለግል ነው፡ የቅድመ ትምህርት የማንባብ ፈተና የተዘጋጀው የተማሪዎችን የቅድመ የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል የማጠቃለል ብልሀትን ለሚፈተሸና ለማየት ሲሆን የድህረ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናው የተዘጋጀው ደግሞ የሙከራ ቡድኑንና የቁጥጥር ቡድኑን ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክህሎት የማጠቃለል ብልሀትን በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት እና ከቅድመ ምንባብ ፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ልዩነት ለማየት ነው፡

ሁለቱም ፈተናዎች የተዘጋጁት አጠቃላይ የምንባብ ሀሳብን፣ ከምንባቡ የወጡ ዝርዝር ሀሳቦችን ባካተተ መልኩ ነው፡ ፈተናው አስተማማኝና ትክክለኛነት እንዲኖረው ማለትም የቃላት ግድፈት፣ የዓረፍተ ነገር ውስብስብነት፣ አሻሚነት ያለው መልስ እና የቃላት እሚያያዊና ፍካሪያዊ ፍች ባላቸው ቃላት ምክንያት እና የአፃፃፍ ግድፈት ምክንያት የሚፈለገውን መልዕክት ሳያስተላልፍ እንዳይቀር ለአቻ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ካሉ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ቀርቧል፡፡ ከዚያም ከተፈታኝ ተማሪዎች በተገኘው መረጃ ጥያቄው ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች ካሉበት ተማሪዎች ጥያቄውን እንዲከቡት እና ዝርዝር መረጃ እንዲሰጡ ከወረቀቱ የታችኛው ህዳግ ላይ እንዲፅፉ ቦታ ተትቶላቸዋል፡፡ በዚህ መሰረትም አስተማማኝነቱ በእኩልነት ከፋይ ዘዴ(split Test) ተፈትሿል፡፡ ይህም ዘዴ የቅድመ ሙከራ ጥናት ይባላል፡፡ ይህን ፈተና ከላይ የቀረበውን ሂደት ካጠናቀረ በኋላ የተዘጋጀው ፈተና በአማካሪ ከተገማገሚ

አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመጨረሻም የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ሁለት መምህራን አማካይነት ታርሞ የሁለቱን አማካይ ውጤት በመውሰድ ለውጤቱ ትንተናው አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

### 3.3.2 ቃለ መጠይቅ

በጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋለው ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ-መጠይቅ ሲሆን አላማውም የማጠቃለል ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ግለ-ግምገማ ለማወቅ ነው፡ በቃለ መጠይቁ አምስት ጥያቄዎች የተካተቱ ሲሆን የጠያቂውን ግለ-ሀሳባዊነት /subjectivity/ ለመቀነስ በአይነታቸው ነጻ ጥያቄዎች ሆነው ቀርበዋል፡፡

የቃለ መጠይቆቹን ትክክለኛነት (validity) ለማረጋገጥ ሲባልም ጥያቄዎቹ ከተዘጋጁ በኋላ ምርምሩ በተካሄደበት አካባቢ የቋንቋ መምህራንን በማሳየትና ሀሳባቸውን በመቀበል፣ ጥያቄዎችን የሚፈልገውን ባህሪ ለማሳካት እንዲያስችሉ ተፈላጊው ማስተካከያዎች ተደርጎባቸዋል፡፡ ለዋናው ጥናት ከመዋላቸው በፊት በጥናቱ ላልተካተቱ ሶስት መምህራን ላይ ተሞክረው የሀሳብ ግልጽነታቸው፥ የቋንቋ ቀላልነታቸውና ተፈላጊውን መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉ መሆናቸው ተረጋግጦ በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ በተመረጡ አራት መምህራን የዋናውን ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ስራ ላይ ውሏል፡፡ ቃለ መጠይቁ የተካሄደው የሚያውቁ ደምፅ በሌለበት ክፍል ሲሆን እያንዳንዱ ተጠያቂ በአማካይ 15 ደቂቃ ወስዷል፡፡

## 3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ተፈላጊው መረጃ ከተሳታፊዎች በፈተና ከተሰበሰበ በኋላ በስርዓት ይደራጃል፡፡ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ በስርአት ከተደራጀ በኋላ በሁለቱ አማካይ ውጤት ልዩነት ይኖረው እንደሆን ለማረጋገጥ ውጤቱ የባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ( Independent sample t-test) ተሰልቶ ተተንትኗል፡፡ በዚህም መሰረት በፈተና የተገኘው የተማሪዎች ውጤት የነጻነት ደረጃውና የጉልህነት ደረጃውን እንዲሁም የቲ-ዋጋን ጨምሮ የተገኘው ውጤት በማወዳደር የተደረሰበት ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡ ይህም የመረጃ መተንተኛ ዘዴ በጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ የቀረበውን በሙከራና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የማንበብ ክሂል የማጠቃለል ብልሀት ላይ ያለውን ፋይዳ ለማረጋገጥ ይሆናል፡፡ እንዲሁም

በእያንዳንዳቸው ቡድኖች በየራሳቸው መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት የቅድመና የድህረ ትምህርት ውጤቶችን መሰረት በማድረግ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ–ቴስት ( Dependent sample t-test) ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## 3.5 የ ጥናቱ ሂደት

የዚህ ጥናት መሠረታዊ ዓላማ የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነበር፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ ጥናቱ በሚከተለው መንገድ ተከናውኗል፡፡

የጥናቱ ሂደት ተገቢ የሆነውን መንገድ እንዲከተል በመጀመሪያ ለጥናት የተመረጠው ትምህርት ቤት በማግኘት በእጣ ናሙና የተለዩትን ክፍሎች መምህራን ፈቃድ ተወስዷል፡፡ በቀጣይ ለዚህ ጥናት የተመረጡትን ተማሪዎች በአካል በማግኘት በቀጣይ የመማር ማስተማር ሂደት በመማር ማስተማሩ ክፍለ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር እንደመጣ በመግለፅና ዓላማውን ግልፅ በሆነ መንገድ በማስረዳት ወደተግባር ተገብቷል፡፡ በቀጣይም የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ የሆነውን ፈተና ጥያቄ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህም ጥያቄ የቅድመ ትምህርት ፈተና ነው፡ ከዚያም የተዘጋጁት ጥያቄዎች አስተማማኝነታቸውን ለማረጋገጥ የዚህ ጥናት አማካሪን የተዘጋጁትን ምንባቦችና ጥያቄዎች በማስገምገም በተጨማሪም በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ከአጋር መምህራን ተጨማሪ ግብዓት በመውሰድ ማሻሻያ በማድረግ ለፈተና ቀርበዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የሙከራና የቁጥጥር ክፍሎች ተመሳሳይ በሆነ ጊዜና የጊዜ ርዝመት በተመሳሳይ ጊዜ ተሰጥተዋል፡፡ ከዚያም የፈተና ወረቀቶቹ ተሰብስበው በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ሦስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካኝነት ታርሞ የሦስቱን መምህራን አማካይ ውጤት በመውሰድ በውጤት ትንተናው አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ይህም የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ያላቸውን ደረጃ ለማየት ነው፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑን የመጀመሪያው ደረጃ ከሆነው የቅድመ ትምህርት ፈተና መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ በተመደበላቸው የመማር ማስተማር ሂደት በተቃራኒ ፈረቃ በሳምንት ሁለት ክፍለጊዜ ለማስተማር አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥናት በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦችን ለማስተማሪያነት ተዘጋጅተዋል፡፡

በሙከራው ጥናት የትግበራ ወቅት ተማሪዎች ሁለቱንም ቡድኖች ከሚያዚያ 15 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ.ም ለአራት ሳምንታት ( ለ8 ክፍለ ጊዜያት፤ አንድ ክፍለ ጊዜ 40 ደቂቃ ነው) አንብቦ የሚረዳት ትምህርት ለሙከራ ቡድን የማዳቀለል ብልሀትን ብቻ ለቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ ሚደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት በመከተል ተምረዋል፡፡ ለዚህ ያመች ዘንድ ለሁለቱም ክፍል ከዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ከቀረቡት ምንባባት መካከል ወንድማማቾቹ፣ አካባቢያችን፣ ማናኛ ብዙሀንና ምርጥ ንግግር የሚሉትን ርዕስ በማምረጥ ለማስተማሪያነት አውሏል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### 4.1. የውጤት ትንተና

ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው ተማሪዎች የማዳቀለል ብልሀት ለአንብቦ ሚረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡ ይህን ለማካካት በፈተና፣ በቃለ መጠይቅ በተሰበሰቡት ሚረጃዎች የማዳቀለል ብልሀት ለአንብቦ ሚረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ፋይዳ ምን ይመስላል? የማዳቀለል ብልሀት በወንደና በሴት ተማሪዎች የአንብቦ ሚረዳት ውጤት ልዩነት ይኖር ይሆን? የሚሉት መሠረታዊ የምርምሩ ጥያቄዎች ተተንትነዋል፡፡

#### 4.1.1. የ ፈተና መረጃ ትንተና

የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ሚና ምን ይመስላል? ለሚለው የጥናቱን የመጀመሪያ መረጃዎች በገላጭ ደምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትኗል፡፡ የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ሚና ምን እንደሆነ በቅድመ ፈተናና በድህረ ፈተና በተሰበሰበው መረጃ አማካዩና መደበኛ ልይይቱ ተሰልቷል፡፡ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለማረጋገጥ የዳግም ልኬት ናሙና ቲ–ቴስት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

በመጨረሻም በዳግም ልኬትና በባዕድ ናሙና ቲ–ቴስት የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር ወይም ለማጣጣር በነጻ ቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በገለፃ ተተንትኗል፡፡ እነዚህ ከመምህራን የተሰበሰቡ ቃለ መጠይቆች የሚያገለግሉት በዳግም ቲ–ቴስትና በባዕድ ናሙና ቲ–ቴስት የተገኙትን መረጃዎች ለማጠናከር ነው፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ትንተና የሚደረገው በተማሪዎች መካከል የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ የመረዳት ክሂል ላይ ልዩነት መኖሩን ማንዘብ ነው፡ ይሄውም በቅድመ ትምህርት የተገኘው ውጤት ተቀራራቢ መሆኑን ይተነተናል፡፡ ለዚህም በፈተና የተገኘው መረጃ ትንተና በገላጭ ስታስቲክስና በባዕድ ናሙና ልኬት ቲ–ቴስት (Independant measure sample t-test) ተሰልቷል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 4.1ና 4.2 የተመለከተው ይመስላል፡

ሰንጠረዥ **4. 1**፡ –የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ትንተና በነፃ ናሙና ገላጭስታስቲክ

| ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 58 | 6.14 | 1.744 | .244 |
| የቁጥጥር ቡድን | 60 | 5.76 | 1.595 | .223 |

የሙከራ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (6.14) ከቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ

ውጤት (5.76) በ0.38 በልጦ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብሌሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ሚዛን ልይይት (1.744) ከቁጥጥር ቡዶች የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብሌሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ሚዛን ልይይት (1.595) በ0.149 በልጦ መገኘ ኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ይሁን እንጂ የሁለቱም ቡድኖች ቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት የሌለው ወይም ተቀራራቢ (ተመሳሳይ) ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የሙከራ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብሌሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብሌሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በ0.38 እንደ በለጠ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በመካከላቸው ላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ርግጠኛ ለመሆን ግን ደምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.2 እንደተመለከተው የነፃ ናሙዎች ቲ–ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

**ሰንጠረዥ 4. 2፡ – የሁለቱም ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ማጠቃለል ብሌሀት የአንብቦ መረዳት ፈተና የነፃ ናሙና ቲ–ቴስት ልኬት**

| ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | የነጻነት ደረጃ | የ "ቲ" ዋጋ | ጉልህነት (sig. 2-tailed |
|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 58 | 6.14 | 116 | 0.3075 | .915 |
| የቁጥጥር ቡድን | 60 | 5.76 | | | |

፡፡P > 0.05

(ቲ(116)=0.3075፤ ፒ>0.915)

ሠንጠረዥ4.2. የተመለከተው የሁለቱ ናሙና ቲ–ቴስት በሁለቱም ስሌት እንደሚሳየው ፈተናውን የወሰዱ ሃምሳ ስምንት የሙከራ ቡድንና ስልሳ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል

ብልሃት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘው የቲ–ዋጋ በመቀረጎምና ውሳኔ ላይ ለመድረስ ደረጃዎችን ማቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የምላሙ አይነት አቅጣጫየለሽ ነው፡ ይህም (ቲ(116)=0.3075፤ፒ>0.915)

በመቀጠል የተገኘው የቲ– ቴስት ዋጋ ከጉልነት ደረጃው ዋጋ ጋር በማውዳደር ለምላሙ ምላሽ ማስጠት ይሆናል፡፡የተገኘው የቲ–ቴስት ዋጋ 0.3075 ሲሆን የእኩልነት ደረጃው ደግሞ 0.915 ነው፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ የሁለቱ ቡድኖች የቲ–ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት የጉልነት ደረጃ ዋጋ ያነሰና አማካኝ ውጤታቸውና መደበኛ ልይይታቸው ስንመለከት የጎላ ልዩነት እንደሌለው ስሌቱ ያሣያል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች የአንብቦ መረዳት የማቃለል ብልሀት መሠረታዊ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ **4. 3**. የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምሮት ማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ትንተና በዳግም ልኬት ገላጭስታስቲክ

| ቡድን | የናሙና ብዛት | ፈተና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 58 | ቅድመ ትምህርት | 6.14 | 1.744 | .244 |
| | | ድህረ ትምህርት | 7.75 | 1.695 | .232 |

የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት የማጠቃለል ብልሀት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (7.75) ከቅድመ ትምህርት የማንበብ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (6.14) በ1.61 በልጦ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኖች ቅድመትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (1.744) ከድህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (1.659) በ0.085 በልጦ ማነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑ የሙከራ ቡድኖች ቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ከላይ በቀረበው ትንተና የሙከራ ቡድኖች የድህረ

ትምህርት የማዳመጥ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት የማዳመጥ ብልሀት የአንብቦ ሚዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በ1.61 እንደበለጠ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ደምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.5 እንደተመለከተው በዳግም ልኬት ቲ–ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.4. የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የማዳመጥ ብልሀት የአንብቦ ሚዳት ፈተና በዳግም ልኬት ናሙና ቲ–ቴስት**

| ቡድን | የናሙና ብዛት | ፈተና | አማካይ ውጤት | የነጻነት ደረጃ | የ "ቲ" ዋጋ | ጉልህነት (sig. 2-tailed |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 58 | ቅድመትምህርት | 6.14 | 57 | -454 | .000 |
| | | ድህረትምህርት | 7.75 | | | |

፡፡ P < 0.05

(ቲ(57)= -454፡ ፒ>0.000)

ሠንጠረዥ4.4. የተመለከተው የሙከራ ቡድን ቲ–ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው ፈተናውን የወሰዱ ሃምሳ ስምንት የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የማዳመጥ ብልሃት የአንብቦ ሚዳት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘውን የቲ–ዋጋ በማተርጎም ውሳኔ ላይ ለመድረስ ደረጃዎችን መከተል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህውም (ቲ(57)=-454፡ ፒ>0.000)

በመቀጠል የተገኘውን የቲ– ቴስት ዋጋ ከጉልነት ደረጃው ዋጋ ጋር በማወዳደር ለምላሙ ምላሽ መስጠት ይሆናል፡፡የተገኘውን የቲ–ቴስት ዋጋ -454 ሲሆን የእኩልነት ደረጃው ደግሞ 0.000 ነው፡፡ ወደ ማጠቃለያው ሲመጣ በሙከራ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና የቲ–ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት የጉልነት ደረጃ ዋጋ ያነሰና አማካኝ ውጤታቸውንና ሚዛናዊ ልይይታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት እንደሌለው ስሌቱ

ያሣያል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ትምህርትና በደህረ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የማጠቃለል ብልሃት የአንብቦ መረዳት ኪሂል ችሎታ መሠረታዊ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 4.4 በሙከራ ቡድኖች የደህረ ትምህርትና የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ መረጃው በዳግም ልኬት ናሙና ቲ–ቴስት ተሰልቶ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t(57)=-.454, p=.000) አሳይቷል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ትምህርትና በደህረ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ መሠረታዊ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ **4. 5** የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርትና የደህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ትንተና በዳግም ልኬት ገላጭ ስታስቲክ

| ቡድን | የናሙና ብዛት | ፈተና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር ቡድን | 60 | ቅድመትምህርት | 5.76 | 1.595 | .223 |
| | | ደህረትምህርት | 6.04 | 1.311 | .184 |

የቁጥጥር ቡድኖች የደህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (6.04) ከቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (5.76) በ0.28 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኖች ቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (1.595) ከደህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (1.311) በ0.284 በልጦ ማየት ኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የቁጥጥር ቡድኖች ቅድመ ትምህርትና የደህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ልዩነት ያለው ነው ማለትይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የቁጥጥር ቡድኖች የደህረ ትምህርት የማንበብ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በ0.28 እንደበለጠ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ደምዳሚዊ

ስታትስቲክስ ማቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.6 እንደተመለከተው በዳግም ልኬት-ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሰንጠረዥ **4. 6.** የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የምንባብ ፈተና በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | የናሙና ብዛት | ፈተና | አማካይ ውጤት | የነጻነት ደረጃ | የ "ቲ" ዋጋ | ጉልህነት (sig. 2-tailed |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር ቡድኖች | 60 | ቅድመትምህርት | 5.76 | 59 | - 0.170 | .032 |
| | | ድህረትምህርት | 6.04 | | | |

:: P < 0.05

(ቲ(59)= -.170:ፒ<0.32)

ሠንጠረዥ4.6. የተመለከተው የቁጥጥር ቡድን የቲ-ቴስት ስሌት እንደሚያሳየው ፈተናውን የወሰዱ ስልሳ የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ባይባልም በመካከላቸው ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘውን የቲ-ዋጋ በማርጎም ውሳኔ ላይ ለመድረስ ደረጃዎችን ማቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህውም (ቲ(59)= -.170:ፒ<0.32)

በመቀጠል የተገኘውን የቲ- ቴስት ዋጋ ከጉልነት ደረጃው ዋጋ ጋር በማወዳደር ለምላሙ ምላሽ ማሰጠት ይሆናል፡፡የተገኘውን የቲ-ቴስት ዋጋ -.170 ሲሆን የእኩልነት ደረጃው ደግሞ 0.32 ነው፡፡ ወደ

ማጉቃለያው ሲሞካ በቁጥጥር ቡድኑ የቅድሞ የደሀረ ትምህርት ፈተና የቲ–ቴስት ዋጋ ከተቆረጠለት የጉልነት ደረጃ ዋጋ ያነሰና አማካኝ ውጤታቸውዓና ሞደበኛ ልይይታቸውዓ ስንማለከት የጎላ ልዩነት እንደሌለው ስሌቱ ያሣያል፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑ በቅደሞ ትምህርትና በደሀረ ትምህርት ከተሞኁ በኋላ የማጉቃለል ብልሃት የአንብሞ ሞረዳት ኪሂል ችሎታ ማጡ ኛ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ **4. 7**፡ – የሞኮራዊ ቡድንና የቁጥጥር ቡድኑ የደሀረ ትምህርት የማጉቃለል ብልሀት የአንብሞ ሞረዳት ፈተና ውጤት ትንተና በነፃ ናሞና ገላጬስታስቲክ

| ቡድን | የናሞና ብዘት | አሞካይ ውጤት | ሞደበኛ ልይይት | ሞደበኛ የአሞካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| የሞኮራ ቡድን | 58 | 7.75 | 1.659 | .232 |
| የቁጥጥር ቡድን | 60 | 6.04 | 1.311 | .184 |

የሞኮራ ቡድን የደሀረ ትምህርት የማጉቃለል ብልሀት የአንብሞ ሞረዳት ክሂል ፈተና አሞካይ ውጤት (7.75) ከቁጥጥር ቡድን ደሀረ ትምህርት የማጉቃለል ብልሀት የአንብሞ ሞረዳት ችሎታ ፈተና አሞካይ ውጤት (6.04) በ1.71 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የሞኮራ ቡድን ደሀረ ትምህርት የማጉቃለል ብልሀት የአንብሞ ሞረዳት ችሎታ ፈተና ሞደበኛ ልይይት (1.659) ከቁጥጥር ቡድን ደሀረ ትምህርት የማጉቃለል ብልሀት የአንብሞ ሞረዳት ችሎታ ፈተና ሞደበኛ ልይይት (1.311) በ0.348 በልጦ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በሞሆኑም የሁለቱም ቡድኖች ደሀረ ትምህርት የማጉቃለል ብልሀት የአንብሞ ሞረዳት ችሎታ ውጤት ከአሞካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ ከፍተኛ ልዩነት አለው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የሞኮራ ቡድን ደሀረ ትምህርት የማጉቃለል ብልሀት የአንብሞ ሞረዳት ችሎታ ፈተና አሞካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ደሀረ ትምህርት የማጉቃለል ብልሀት የአንብሞ ሞረዳት ችሎታ ፈተና አሞካይ ውጤት በ1.71 በከፍተኛ ደረጃ እንደበለጠ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በሞካከላቸው ስላለው ልዩነት

የጉልህነት ደረጃ ርግጡኛ ለመሆን ግን ደምዳሚዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.9 እንደተመለከተው የነፃ ናሙዎች ቲ–ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሰንጠረዥ **4. 8** የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የደህረ ትምህርት የማንቃለል ብልሀት የአንብ ሚዳት ችሎታ ፈተና የነፃ ናሙ ቲ–ቴስት ልኬት

| ቡድን | የናሙ ብዛት | አማካይ ውጤት | የነጻነትደረጃ | የ "ቲ" ዋጋ | ጉልህነት (sig. 2-tailed |
|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 58 | 7.75 | 116 | 2.300 | .003 |
| የቁጥጥር ቡድን | 60 | 6.04 | | | |

፡፡P < 0.05

(ቲ(116)=2.300:ፒ<.003)

ሠንጠረዥ 4.8. የተመለከተው የሁለቱ ናሙ ቲ–ቴስት ስሌት እንደሚሳየው ፈተናውን የወሰዱ ሃምሳ ስምንት የሙከራ ቡድንና ስልሳ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል የደህረ ትምህርት የማንቃለል ብልሃት የአንብ ሚዳት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የተገኘውን የቲ–ዋጋ በመተረጎምና ወሳኔ ላይ ለመድረስ ደረጃዎችን መከቀሙ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይኸውም (ቲ(116)=2.300:ፒ<.003)

በመቀጠል የተገኘውን የቲ– ቴስት ዋጋ ከጉልነት ደረጃው ዋጋ ጋር በማወዳደር ለምላሙ ምላሽ መስጡት ይሆናል፡፡የተገኘውን የቲ–ቴስት ዋጋ 2.300 ሲሆን የእኩልነት ደረጃው ደግሞ 0.003 ነው፡፡ ወደ ማንቃለያው ሲመጣ የሁለቱ ቡድኖች የቲ–ቴስት ዋጋ ከተቆረጡለት የጉልነት ደረጃ ዋጋ የበለጠና አማካኝ ውጤታቸውንና ሚደበኛ ልይይታቸውን ስንመለከት የጎላ ልዩነት መኖሩን ስሌቱ ያሣያል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች በማንቃለል ብልሀት የአንብ ሚዳት ላይ የመማር ማስተማር ሂደት በታየው ውጤት የማንቃለል ብልሃት የአንብ ሚዳት ችሎታ መሠረታዊ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

### 4.1.2. የ ቃለ ማጠየቅ ትንተና

በቃለ ማጠየቅ ውይይት የተሰበሰበት መረጃዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማጠቃለል ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ያለው ፋይዳ ምን ይመስላል? የሚለውን የምርምሩን ጥያቄ መሰረት አድርጎ እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡ በቃለ ማጠየቁ በመጀመሪያ ለተጠያቂዎች የቀረበው ጥያቄ የንባብ ክሂልን ሲያስተምሩ አዘውትረው የሚጠቀሙት የትኛውን የንባብ ሂደት ነው? ለምን? የሚል ሲሆን አራቱም መምህራን ሦስቱን የንባብ ሂደት ማለትም ቅድመ ንባብ፣ ሂደት– ንባብ እና ድህረ ንባብ ሂደቶችን እንደሚከተሉ ገልፀዋል፡፡

ሁለተኛው ቃለ ማጠየቅ በንባብ ክሂል ትምህርት ጊዜ ለማስተማር ቀላል ነው ብለው የሚያስቡት ሂደት የትኛው ነው? ለሚለው ጥያቄ ሦስቱ መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት በማንበብ ክሂል ቀላልና ከባድ የሚል ደረጃ አለመኖሩን ጠቁመዋል፡፡

መምህርት አንድ ቃል ደግሞ ቀጥሎ ያለው ነው፡ በንባብ ክሂል ትምህርት ጊዜ ለማስተማር ቀላል ነው ብዬ የማስበው ቅድመ ንባብ ሂደትን ነው ካሉ በኋላ ምክንያቱን ሲገልፁ በቅድመ ንባብ ሂደት ጊዜ ተማሪዎች የቅድመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን የሚነዝሩበትና ለንባብ ሂደቱ የሚዘጋጁበት ሲሆን ከባድ ሂደት የምለው ደግሞ ሂደት–ንባብን ነው ብለዋል፡፡ ምክንያቱን ሲገልፁም ተማሪዎች በአብዛኛው እንዲያነቡ የማደርገው በግል በመሆኑ ፈጣን ተማሪዎች ቀድመው አንብበው ከጨረሱ በኋላ ትዕዛዜን ባለመስማት ቀጣዩን አንቀፅ ማንበብ ስለሚጀምሩና እኩል ስለማይጨርሱ በእኩል ለማስኬድ ከባድ ነው ብለዋል፡፡ ድህረ ንባብ ግን ሁሉም ከጨረሱ በኋላ የሚፈጸም በመሆኑ አስቸጋሪ አይደለም ብለዋል፡፡ እኚህ መምህርት ሂደት ንባብ ላይ የሚጠቅሙን መሣሪያ ወይም መፅሐፍ ላይ ያለውን ትዕዛዝ በአግባቡ አላስተላለፉም፡፡ መልዕክቱን የማስተላለፍ ድክመት እንዳለባቸው ያሳያል፡፡

ሦስተኛው ቃለ ማጠየቅ ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደት የማንበብ ክሂልን ሲያስተምሩ የተማሪዎች የማጠቃለል ብልሃት ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ አራቱም መምህራን ሲመልሱ የተማሪዎች የማጠቃለል ብልሃት ለማንበብ ካላቸው ፍላጎት አንፃር የሚወሰን ሲሆን ለምንባብ ትኩረት ሰጠው የሚያነቡ ተማሪዎች የምንባቡን ሀሳብ

ተረድተው የማጠቃለያ ሀሳብ ለማስጠት እንደሚቸገሩ ነገር ግን ለማንበቡ ትኩረት የሚሰጡት ግን የማንበቡን የማጠቃለያ ሀሳብ ማፍ ወይም ማገር እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡

አራተኛው ቃለ መጠይቅ የተማሪዎች የንባብ ፍላጎት (የማጠቃለል ብልሃት) የመምህ ፍላጎት በማህሩ ጥረትና አቀራረብ ይወሰናል ብለው ያምናሉ? ለሚለው ጥያቄ አራቱም

መምህራን ሲመልሱ በመምህ ማስተማር ሂደት የማጠቃለል ብልሃት በማህራን የትምህርት አሰጣጥ አንፃር የሚወሰን ሳይሆን በተማሪዎች ፍላጎት የሚወሰንና የሚለካ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በአጠቃላይ በቃለ መጠይቁ የማጠቃለል ብልሃት ለአንብቦ መረዳት በመምህ ማስተማር ሂደቱ በማንበብ ክሂል ቀላልና ከባድ የሚባል ደረጃ አለመኖሩን ጠቁመዋል፡፡ በተማሪዎች የማጠቃለል ብልሃት ለማንበብ ካላቸው ፍላጎት አንጻር የሚወሰን መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በመምህ ማስተማር ሂደት የማጠቃለል ብልሃት በማህሩ/ሯ/ የትምህርት አሰጣጥ የሚወሰን ሳይሆን በተማሪው ፍላጎት የሚወሰንና የሚለካ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በመጨረሻም በተማሪዎች መካከል ባለው ልዩነት ከፆታ አንፃር ሲታይ ሴት ተማሪዎች ለማጠቃለል ብልሃትም ሆነ ለአንብቦ መረዳት ከወንድ ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው ተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ሚና መመርመር ነው፡ በመሆኑም በፈተና በተሰበሰቡት መረጃዎች በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታን ማሳልበት ረገድ ያላቸውን ሚና ለሚፈተሽ መረጃዎች በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታቲስቲክሶች ተተንትነዋል፡፡

በዚህ ጥናት በመጀመሪያ የታየው ትንተና ወደ መምህ ማስተማሩ ከማባቱ በፊት የተማረጡት ሁለቱ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖችን ለማየት የሚያስችል የቅድመ ትምህርት ፈተና በሚፈተን ተማሪዎችን በማየት ወደ መምህ ማስተማሩ የሚያስገባ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በዚህም መሰረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ምንም ዓይነት የአንብቦ መረዳት የማጠቃለል ብልሀት ችሎታ ልዩነት አለመኖሩን አረጋግጧል፡፡

የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ዓላማ "የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ ለመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና መመርመር፡፡" የሚል ነበር፤ ዓላማውንም ለማሳካት መረጃው በገላጭ በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡

መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት መሰረትም እንዳሳየው የሙከራ ቡድኖች ድህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና አማካይ ከቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት አማካይ ውጤት በልጦ (ሠንጠረዥ 4.3) ልዩነት አሳይቷል፡፡ ልዩነቱም ጉልህ መሆኑ (ሠንጠረዥ 4.4) ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የቁጥጥር ቡድኖች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ክሂል የድህረ ትምህርት ፈተናው እንደሚያሳየው አዎንታዊ ውጤት እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በጥናቱ ውጤት መሰረት የማጠቃለል ብልሀት የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ መሻሻል የታየው ከምንባቡ የወጡ ቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ በመውጣት፣ ከምንባቡ ዋና ሀሳብ በማየት፣ ከምንባቡ ሀሳብ በማሳት በፅሁፍና በቃል ሀሳብን መግለፅ ለማስተማሪያነት የቀረቡ ፅሁፎች ዋና ዋና ሀሳብን ለማየት አመቺ በመሆናቸው፣ የፀሀፊውን መልዕክት ማየትና መረዳት፣ ከተሰጠው ፅሁፍ በማሳት ማጠቃለያ መስጠት፣ ሀቅና የግል አስተያየቶችን ለማየት ግልጽ በመሆናቸው ለዚህ ውጤት አብቅቷቸዋል ቢባል ምክንያታዊነት ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት ሲታይ የሙከራ ቡድኖች የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ያላቸው ችሎታ የበለጠ ነው፤ የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡ ይህም የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት በስታቲስቲክስ ጉልህ ሆኖ ማግኘቱ አንድ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ የድህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ከቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ሆኖ መታየቱ ተጨማሪ አስረጅ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ጥናት የቁጥጥር ቡድኖች የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ያላቸው ችሎታ ጥሩ ነው፤ የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡ ይህም የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት በስታቲስቲክስ ጉልህ ሆኖ ማግኘቱ አንድ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ የድህረ ትምህርት ችሎታ ከቅድመ ትምህርት ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ሆኖ መታየቱ ተጨማሪ አስረጅ ሊሆን ይችላል፡፡ በአጠቃላይ በዋናነት በዚህ ጥናት

የተገኙ ውጤቶች የመጻፊ በድኑ ከቁጥጥር በድኑ የተሻለ የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ አላቸው ለማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሁለቱ ፆታ መካከል ልዩነት ይኖር ይሆን የሚለውን ሀሳብ ስንመለከት በመጻፊ በድኑ ውጤቱ መሰረት የሴቶች የማጠቃለል ብልሀት ከወንዶች የማጠቃለል ብልሀት የተሻለ ነው ለማለት ያስችላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሔ

### 5.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና አላማ የተማሪዎች የማጠቃለል ብልሀት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸው የታለሙ መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፤

(1) የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ ለመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ሚና ምን ይመስላል?

የጥናቱ ተሳታፊዎች በምስራቅ ጎጃም ዞን በብቸና ከተማ በበላይ ዘለቀ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2011 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ከሚገኙ 915 ተማሪዎች መካከል በእጣ ሰጪ ናሙና የተመረጡት የ"9E"ና "9G" ክፍል 118 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ በጥናቱ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያም ፈተና ሲሆን በተጨማሪም ቃለ መጠይቅ ተጠቅሟል የክፍል ደረጃውን መሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፉን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡

ተጠኚዎችም በመደበ ማስተማሩ ሂደት በተመረጡ ምንባብ ከማስተማር በፊት የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ መረዳት ፈተና በጥናቱ አመቻሪና በሌሎች ባለሙያዎች ማስተካከያ ታክሎበት፣ በመጻፊ ጥናት ተፈትሾ አስተማማኝ ሆኖ በማግኘቱ የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂልን ለማለካት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመቀጠልም ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በማስተማሪያነት የተዘጋጁትን ማስተማሪያ ፅሁፎች ለአራት ሳምንት ወይም ስምንት

ክፍለ ጊዜ ሲሞሉ ቆይተዋል፤ በመጨረሻም ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር አቻ የሆነ የድህረ ትምህርት ፈተና ተግባራዊ በማድረግ ለጥናቱ የሚፈለገው መረጃ ተሰባስቧል፡፡

በፈተና አማካኝነት የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ በዋናነት የዚህ ጥናት ጉዳይ የሆነውን የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ ለመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ፋይዳ /አስተዋጽኦ/ ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ በቅድመ ትምህርት ፈተናና በድህረ ትምህርት የተገኘውን መረጃ በባዕድ ናሙና ቲ–ቴስት ተተንትኗል፡፡ በዚህም የቅድመ ትምህርት ፈተና በሙከራና በቁጥጥር ቡድኖች ላይ አማካይ ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ ምንም ልዩነት ያልታየበት በመሆኑ ለመማር ማስተማሩ የተመረጡት ተማሪዎች በማጠቃለል ብልሀት ያላቸው ደረጃ ተመሳሳይ መሆኑንና ለጥናቱ መነሻ የሚሆን በመሆንና ለማስተማር የሚያስችል መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ክፍል የታየው በድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘው መረጃ ትንተና እንደሚያሳየው የዚህ ጥናት በመጀመሪያ ይዘት የተነሳው መሪ ጥያቄ የማጠቃለል ብልሀት አንብቦ ለመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ፋይዳ /አስተዋጽኦ/ ምንድን ነው? የሚል ነበር፡፡ በቅድመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት የፍላጎት መረጃ መሰረት በተሳታፊዎች የቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት አማካዮች መካከል በዳግም ልኬት ናሙና ቲ–ቴስት መሰረት በስታቲስቲክስ ጉልህ ($p<0.05$) ልዩነት ታይቷል፡፡ በዚህም በሙከራዊ ቡድኖች የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ለውጥ እንዳመጣ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ትንተና መሰረት የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ የተሻሉ እንደሆኑ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ በአንብቦ መረዳት ላይ ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ያሳያል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

1. የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አስተዋፅኦ እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም በአንብቦ መረዳት ላይ የማጠቃለል ብልሀት በአንብቦ መረዳትን በማዝ ረገድ ሚና አለው የሚል እንድምታ ይኖረዋል፡፡

### 5.3 መፍትሔ

በዚህ ጥናት የተደረሰባቸውን ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ ብሎም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማሳደግ እንዲቻል የሚከተሉት መፍትሔዎች ተጠቁመዋል፡፡

1. በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ሚመጣቸው የማጠቃለል ብልሀትን በሚያግዙ መልኩ ቢመረጡ፡

2. መምህራን ለማጠቃለል ብልሀት በማንበብ ክሂል ያላቸውን ጠቀሜታ ተገንዝበው፣ የማጠቃለል ብልሀትን በየክፍለ ጊዜው ቢያስተምሩ፤ ተማሪዎችም ከመማር ማስተማሩ ሂደት በተጨማሪ በሚያነቡበት ጊዜ መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን ሀሳቡም ያታዎች ተገቢውን ትኩረት ቢያደርጉ፡፡

3. በሁለቱም ፆታዎች በማጠቃለል ብልሀት ዙሪያ ግምት ውስጥ ያስገባና ያነፃፀረ ጥናት ወደፊት ቢካሄድ የተሻለ ግንዛቤና የአሰራር ስልት ሊገኝ ይችላል፡፡

## ዋቢ ፅሁፎች


ሚኒሽ ፀጋዬ ፡፡ (2004)፡፡ "የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፡፡" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፡፡ ያልታተመ፡

ተስፋ ወልደሚካኤል፡፡ (2001)፡፡´´የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመረጡ የአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ አዲስ አበባ፡፡ ያልታተመ፡

ታምሩ ፀጋዬ፡፡ (2008) "በበርትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ፣ ጾታ ተኮር ጥናት፡" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡ ያልታተመ፡

ኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስተር እና የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ፡ (2007)፡፡ የአምስተኛ ክፍል የተማሪ መጽሀፍ፡ Nova Publication Printed.

ከድር ሰይድ፡ (2009)፡፡ "በአማርኝ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከመርሃ ትምህርት ጋር ያለው ተጣጣማኝ፡" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀርበ ጽሁፍ፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡ ያልታተመ፡

Armbruister, Bonnie.Band.,andobsorn, Jen.H (2002) *Reading Instruction and Assessment*. Understanding the IRA standards: Boston Allyn and Bacon.

Aebersold J.A. and Field. M.A (1997) From Reader to Reading Teachers. Issue and Stratgies for Scond Language Classroom. Cambridge Universitie Press.

Block, C.C. (1997) *Teaching the Language Arts: Expanding Thinking Throught Students Centered Instruction. Boston*: Allyn and Bacon.

Brown, A. L., Day, J. D., & Jones, R. S. (1983).The development for plans for summarizing texts.*Childhood, 54*, 968-979.

Brwon, J.D. (1994). *Princple of Language Learning and Teacing.* New Jersey: Profice Mull Regent.

Carrell, P.L. (1988) Introduction. In P.L. Carrell J. Devine and D.E. Eskey. 73-92.

Clarke, M. (1982). On bandwagons, tyranny, and common sense. *TESOL Quarterly, 16.* 437-448

Conely, M,W (1992) *Content Reading Instruction*.Communication. Approach New York : Mc Graw-Hill Inc.

Collins, A., Brown, J. S., & Larkin, K. M. (1990). Inference in text understanding. In R. J. Spiro, B. C. Bruce, & W. F. Brewer (Eds.), *Theoretical issues in reading comprehension* (pp. 385–404). Hillsdale, NJ: Erlbaum

Denton, C., Bryan, D., Wexler, J., Reed, D. & Vaughn S. (2007), *Effective Instruction for Middle School Students with Reading Difficulties: The reading Teachers' Sourcebook,*

Dole, J.A., Duffy, G.G., Roehler, L.R., and pearson (1991) *Moving from the old to the New*: Research on Reading compherension In struction. "Review of Educational research". 61 (2) 239-264

Edaso Mulut( 2007).An Exploration of Factors Affecting Preparatory I School Students Reading Comprehension Skill :Addis Ababa University institute of language studies department of foreign languages and literature (graduate programme

Grellet, F. (1981) Developing Reading Skills: A Practical Guide to Reading Comprehension Exercises. Melbourne: Cambridge: Cambridge University Press.

GreenWood, J. (1981). "*comprehension and Reading* "in Abbot, G.and Wingard, P. (eds.) Teaching of English as an

International Language; Apractical Guide Edinburgh; Nelson and sons Ltd.

Getachew Asrat. (1996). The teaching of Reading in Government High school in A.A Descriptive study . Unpublished M.A.theses . Addis Ababa University.Addis Ababa.

Harvey, S. & Goudvis, A. (2000). Strategies that work: Teaching comprehension

to enhance understanding. Markham: Pembroke.

Harmer, J. (1991).The practiceof English language. New York.Longman

Heilman, A.W. Blair, T. R. and Ruphley W.H. 1998. Principles and Practice of Teaching Reading. ($9^{th}$ Ed). New Jersy Prints Hall Inc.

Hayland ken(1990). Purpose and strategy. Teaching Extinsive Reading skills. English Teaching forum xxvIII(2/14-17)

Kirby, J. (1988). Styles, Strategies, and Skill in Reading. In R. Schemeck(ed.). (229-274)

Lunzer, E.A. and Gardner, K. (1979). *The Effective Use of Reading*. London: Heineman.

Lindsay. (2006). Teaching and Learning English.Oxford: Oxford University Press.

MeDonugh,J, and Ch shaw (2003).Materials and methods in ELT. Oxford; Oxford University press.

Muller D.L (1992) Teachers Attitude Towards reading. Journal of

Reading.(17) 202-205

Nelson, Gayie. L (1984) *Reading Astudent center Approach*: EnglishTeaching Forum xxII(4) 2-5.

Norton .D.E (1997) The Effective Teaching of Language Arts. ($5^{th}$ Ed). New Jersy. Prentice Hall Inc.

Nuttal, C.(1982). *Teaching reading skills in a foreign language.*London: Heinemann.

Nuttal, C.(2000). Teaching English skills as a Foreign Language: Oxford. Macmillian. Heinemann

O'Malley, J.M. & Chamot, A.U (1990) *Learning strategies in second language acquisition*. Cambridge: Cambridge University Press.

Oxford, R. L. (1990) *Language learning strategies: what every teacher should know*. New York: HarperCollins

Pardo, L. (2004) What Every Teacher Needs to Know About Comprehension. In *The Reading Teacher.*272-281.

Simith, F (1985) Reading.Greating Britain combridge University Press.

Stateman, S. (1981). The Activation of a systematic Theory: A pedagogical Theory in the EFL classroom.Jounal of English Language teaching 35 (3),pp. 232-233.

Tesfu gebre (2015). The effect of strategy instruction on grade elevenstudents' reading comprehension performance: the Case of kulla preparatory school in arsi zone, Oromia region haramaya university, haramaya

USAID (2016). Reading for Ethiopia's Achievement Developed Community Outreach (READ CO) Cooperative Agreement No: AID 663-A-15-00003

Wallace,C.(1992).Language Teaching in Reading. New York. Oxford university press.

Wen den, A. (1992), ***Learner strategies for learner autonomy.*** Englewood Cliffs, NJ: Prentice Hall Regents

Williams, M., & Burden, R.( ***1997). Psychology for language teachers:A social constructivist approach.*** Cambridge, UK: Cambridge University Press,

Williams, E. (1984). *Reading in the Class room*. London: Macmillan publishers, Ltd.

Willig, A. (1989), 'A meta-analysis of selected studies on the effectiveness of bilingual education', *Review of Educational Research* 55, 3, 269-317

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ ክፍል ደህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## አባሪዎች

### አባሪ 1. የቅድመ ትምህርት ፈተና

በብቹና ከተማ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚካሄደው ጥናት የተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ በሚጀነት ለማጠቀም የተዘጋጀ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የቅድመ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት ለተማሪዎች የተዘጋጀ የአንብቦ መረዳት ፈተና፡፡

ቀን ________/ _________ 2011ዓ.ም

የተፈቀደ ጊዜ 1፡30

**ምንባብ አንድ**

**ያበዳሪዋ ጩፄ**

"በጣም ከፉነህ ስለዚህ ነው ችግር የጎለሰሰህ... ግን ምን ታደርግ 'አውራ ዶሮ በየፍጉ ክምር ላይ ቆም ይጮሃል' ... እኔን ተመልከተኝ፤ ለምሳሌ - አዎ፣ እግዜር ማስን ንጉሠ ነገሥቴ ክብርን አልነሱኝም፡ ሆኖም አልኮራም፤ እንዴት ልኮራ እችላለሁ? ማኝና! ትል ለራሴ! ትንሽ ፍጥረት፣ምናምን! ግን እንደምታየው ራሴን ዝቅ ዝቅ በማድረጌ እግዜርና ንጉሤ ከፍ ከፍ አደረጉኝ በፊታቸው... በሰማያዊ ኃይል የጉላበተ እንዲህ ነው ይኸውልህ... እግዜር ማሱን ሰጥቶ በንጉሤ ፊትም ማስ እንዳገኝ አደረገኝ...

"... እና አሁን ታዲያ የመጣኸው ትንሽ ዘንጋዳ ለማበደር ነው አልክ...?"

" ነበራ እሞቴ ማስቸገሬ ባይሆን…"

" ለማግዛት ነው የምትፈልገው…?"

" ከየት እቴ እሜቴ ብሩ ከየት ተገኝቶ? በዚያው ባይነት ለመክፈል ነው እንጂ በትሣሡ…"

" ነገር ማጧጧጫ ገንዘብ አይሆንም፤ ይኸውልህ፣ 'ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው፥ ቀንዱ ይከለክለዋል' ነው"

" መቼም የሚሉት ሳይገባኝ ቀርቶ አይደለም… ብቻ እንዲያው ሰኔና ሰኞ…"

" አዎ ካጡ ወዲያ ማንኛውም ነገር አያምር፤ 'በሰም የተጣበቀ ጥርስ ቢስቁበት አያደምቅ ቢበሉበት አያደቅ…'!"

"ታዲያ ምን ተሻለኝ ይመስልዎታል አሁን…?"

"መከልከሌ አይደለምኮ! 'ሰው ሆኖ የማያብስ እንጨት ሆኖ የማይጨስ'!፣ 'ሰው ከስህተት ብረት ከዝገት…'

"ታዲያ ያሉትን ብለውኝ ብሄድ…"

ብረት ካልፈላ አይላላ' … እንዲህ ልክ ገባህ ይኸውልህ…

"ድሮምኮ ቢሆን … እንዲያው ባንጣጥም ይሆናል…"

"ያለፈው አለፈ፤ አሁን አንድ ልልህ የምፈልገው… ምን ነበር እቴ! አዎ ለሁሉ እግዚአብሔርን…ማለቴ ከሆነ ወዲያ 'ደም ማልቀስ ድንጋይ ማከስ' አያስፈልግም… 'ወረቱን እንደተቀማ ነጋዴ፥ ዋግ እንደመታው ስንዴ' መዋሰስ የወንድ ልጅ ተግባር አይደለም… ያሁኑ ውራት ስህተትህን ማሚሚያ ነው፡ 'ከዝንጀሮ ጋሜ ያንበሳ ማላጣ' መሻሉን ማንዘብያህ … እንዲያ ተንዘጦረህብኝ የነበረው ሰውዬ ቢኖረኝ ነው የማማኸው… 'ተሰካር ያየ ተሜሪ ሸቀጥ ያየ አጣሪ…'

"የሜጃ እጦት ነው እሞቴ…"

"ትዕቢተኛነትህን ትንሽ አብርዶልሃል፤ መቼስ ጨርሶም ባይጠፋ፡፡ አዎ! ለወደፊቱ ማገድ ስንገናኝም ቢሆን ከፊትለፊቴ ሸረር ብለህ ማገዱን ብትለቅልኝ ነወ፸ የለወም፤ አንዳንዴ እንደሚሸልግ ነብር እንዳንዴ እየተፍረገረገ እንደሚጣጣጥ ደመት መሆን ያስተዛዝባል… አዎ ፊት ማጩግ ወይም ማቅንገጩም በእኔ አይደለም… ከግንባርህ ትህትናን አታጥፋ…

"እመቤቴ መቼም ከዚህ በፊት አላስቸገርኩዎትም… "

" እንዴት አዝን ይመስልሃል እንዲህ ተቆራምደህ ሳይ…!"

"ታዲያ ታዝኑ…"

"እንዴታ! በርግጥ ታሳዝነኛለህ፤ ነገር ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ ነው እንጂ 'ህል ያለው ፈርዛዛ ፣ገንዘብ ያለው ቀበዝባዛ' … የተቻለኝን ባደረግሁልህ… እንደምታውቀው ግን ዘንጋዳው ተወደዷል፤ የሚሆንልህ ቢሆን ጥሬው ገንዘብ ይሻለኛ ነበር፡፡ ሳት ሆኗል ዘንጋዳ… እንደ ዘንደሮ ሆኖም አያውቅ… ምን ይመስልሃል ታዲያ…? ደግሞስ ደግሞስ ሰማህ ሆይ፣ ሚዳዳትን የመሰለ ምን ዓለም አለ? ሚዳዳቱ አይከፋም… ዛሬ ባበደርህ ነገ ደግሞ እኔ አበድረኝ ልልህ እመጣ ይሆናል…

" ይሆን ይሆን እመቤቴ … መቼስ…"

" አይ ይሆናል እንኳ ብዬ አይደለም… "ያልጠረጠረ" ለማለት ያህል ነው… እና ታዲያ አሁን የምትፈልገው አስራ አምስት ቁና መሆኑ ነው…?"

"አዎ እመቤቴ ፈቃደዎ ከሆነ…"

" ጥሩ ነው… አስራ አምስት ቁና… ዘጠኝ ቁና እሰጥሃለሁ ማለት ነው፤ በትሣሥ አስራ አምስት አድርገህ ትመልሳለሁ…"

"አይ እኔ እንኳን…"

“ እንደምታየው ወለድ አልፈልግም ያው ዓይነት ባይነቱ ነው፤ በብዘት አምሮተህ ከምታገባው፣ አዎ፣ ብዙ አይደለም፡ ደግሞ በደንብ እየተንቸረፈፈ ይሰፈርልሃል፤ ‘ወዶ የዋጡት ቅልጥም ከፍርምጣ ይጥም

“ትንሽ አልበዛም እሜቴ…?”

“በዛ? አይ እንግዲያው ከበዛ ሌላ ሰው ብትጠይቅ ይሻላል፡፡ እኔ እስከዚህ የምጓጓለት ነገር አይደለም፤ ስላዘኔታዬ ነው የማደርህ፡ – አንተ መጥህብኚ እኔ አልመጣሁብህም…”

“መቼም እሜቴ አዜኔታዎን አልኩ እንጂ…”

“አዘኔታዬ አልተለየህም… ደግማም ነገር ቢዘበዝቡት ምን ያደርጋል…”

“እርግጥ ነው ብቻ የምጠይሰው ትንሽ የበዛ መሰለኝ…”

“አይ፣ አይ፣ አይ፣ እንግዲህ በነገር አትጎሽምጠኝ፡፡ መግስት ከፈቀደልኝ በላይ የምጠስድብህ **አራጣ** በሊታ ሟድርግህ ነው? አጉል ተናገርክ፡፡ እኔ ደሞ ጥንክር ሰው ስትመስለኝ ወስዋሳና ተልካሻ ውጦህ ልበል…?”

“ዋ፣ እሜቴ መቼም ያላቅሜ”

“ምነው ቢገባህ እኔስ በምን ልኑር ትላለህ? ስንት መሰለህ የሚከሰው ጉዳዩ… የየቁረንጨው ግብር ራሴን ሊያዞረው ነው፡ በዚህ ላይ የሮማን ሠርግ ደርሷል… የየማኮሳቱ ድርጎ አለብኝ… ስንቱን ልበልህ… አዎ፣ ባይሆን ለወደፊቱ በየቦታው ከማዝጥዘጥ ጠንከር ብሎ መስራት ይኖርብሃል፡፡ ‘ወስፌ ቢለግም ቅቤ አይወጋም…’

“መቼስ ምን ይደረጋል ይሁና ከጨዉኑ …”

“ጨዉኔ! የምን ጨዉኔ? ጨዉኔን ምን አመጣው…? አይ አድራጎቴ ጨዉኔ ከመሰለህ ብትተወው ይሻላል…”

“ማለቴኮ እሜቴ…”

“ሰማሁኮ ያልከውን…”

"ይሆና እንግዲያው መቼስ ምን አደርጋለሁ...?"

"አዎ! እንዲያ ይሻላል... ዘንድሮ አምኘን አይደለም፤ የምታደርገው ነገር የለም... "በነገራችን ላይ እኔ ላንተ አንድ ነገር ስውልልህ ፣ አንተም ለኔ መዋል ሳይኖርብህ አይቀርም... የክርስቲያን ምልክቱ ነው፡"

/አደፍርስ፣ ከገጽ8-12

***ትዕዛዝ - ከላይ በቀረበው ምንባብ አንብባችሁ ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡***

***1.*** ልበለዱ በየትኛው የአደራረስ ስልት የተጻፈ ነው?

2. በምንባቡ መሰረት አራጣ ምን ማለት ነው?

3. ዘንጋዳው በደንብ እየተንቸረፈፈ <u>**ይሠፍርልሃል**</u>፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው?

4. ባለፈው ዓመት ጠፍ አፍጬ ዋልልኝ ብልህ እንዲያ <u>ተንዠበረህብኝ</u> የሄድከው ሰውዬ ዛሬ ተመልሰህ መጣህ? የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው?

5. አጉል ኩራተኛ ስለሆንህ ችግር <u>ይጎለስስሃል</u>፡፡

6. በምንባቡ ውስጥ በደብልጥ ጎልቶ የሚታየው የዘይቤ ዓይነት የትኛው ነው ምሳሌ ጥቀሱ?

7. የመጀመሪያው አንቀፅ የሚያስረዳው ምንን ነው?

8. በምንባቡ ውስጥ የክርስቲያን ምልክት ነው የተባለው ጉዳይ ምንድን ነው?

9. በምንባቡ ውስጥ ነገር ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ ነው እንጂ ሲል ምን ለማለፅ ፈልጎ ነው?

10. የምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት ምንድን ነው?

## አባሪ 2. የደህረ ትምህርት ፈተና

በብቸና ከተማ በበላይ ዘለቀ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚካሄደው ጥናት የተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ፋይዳ በሚደርነት ለማጥቀም የተዘጋጀ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የደህረ ትምህርት የማጠቃለል ብልሀት ለተማሪዎች የተዘጋጀ የአንብቦ መረዳት ፈተና፡፡

ቀን ________/ _________ 2011ዓ.ም

የተፈቀደ ጊዜ 1፡30

**ምንባብ አንድ**

**ማር ሰውገደለ**

‹‹ ይድረስ ለእናቴ ለወ/ሮ ግምጃ ስላሴ

‹‹ እማዬ ለጠፋሽ እንደምን ከረምሽ? ... እኔ እንዳለሁ አለሁት፡፡ ሰሞኑን በጥሩ ሁናቴ ላይ አይደለሁም ያለሁት፡፡ አዲስ ነገር ስለገጠመኝ ነው ይሄንን አሳዛኝ ደብዳቤ ዛሬ የፃፍኩልሽ፡፡ካንቺ ከናቴ በላይ ማን በዚህ ክፉ ሰዓት ከጎኔ ሊቆም ይችላል? ... የጭንቀቴ ተካፋይ ትሆኚና ከዚህ ጉድ ውስጥ ታወጪኝ ዘንድ እምነቴ ነው እማዬ፡፡ የሆንኩትን ስትሰሚ እንዳትበሳጪ እንዳታዝኚም አስቀድሜ እለምንሻለሁ፡ ይሄውልሽ እንዲህ ሆነ እማዬ...

‹‹ ባለፈው ሳምንት አንድ የሉካንዳ ቤታችን ደምበኛ የጎረሰው ስጋ አንቆት ከሞተ በኋላ፣ የፍቼ ሰው ሁላ በክፉ ዐይኑ ያየኛል፡፡ ሰውየው ከሞተበት እለት ጀምሮ ወደ ሉካንዳ ቤታችን የሚባው ሰው ቁጥር ቀንሷል፡፡ ወሬውን ያልሰሙ አንዳንድ ሰዎች ብልት ብልቱን እየጠያየቁ፣ ከስንት አንዳንዶቻቸው ብቻ አስጠቅልለው ይሄዳሉ፡ የገዛውን ሥጋ እራሱ ማሽከም የተጠየፈውን ደሞ እንደተለመደው እኔኑ አሸክሞኝ ከኋላ ኋላው ያስሮጡኛል፡፡ ጥቂቶቹ ትንሽ ሳንቲም ቢጥሉልኝም፤ አብዛኞቹ ግን በነፃ ነው የሚያሸክሙኝ፡፡ ‹... ልጄ በርታና ትምህርትህን ተማር ...› ያልሽኝን ሁሌም ስለማልረሳ፣ የጋሽ ቶልቻን ቁጣ አዘል ትእዛዝና የሥራ ጫናውን እንግልት እየቻልኩ ፤ በማዘገም ላይ ነኝ፡፡ ታዲያ እማዬ ሰሞኑን የሚያመኝን ጭንቀት የሚያብስብኝ፤ ይሄ ሥጋ አሸክሞ ከኋላ ኋላው የሚያስሮጠኝ ሁሉ ድንገት ቆም ብሎ፤ ‹ ማሞር ማለት አንተ ነህ? ሰውየውን ለምን ገደልከው? ...› ብሎ

የሚያፋጥጠኝ እየመሰለኝ፤ ሰውነቴ በሀሳብ እልቅ ይላል፡፡ አንዳንዱም የገዛውን ሥጋ እቤት ደርሶ ለማብሰል ካለው ጉጉት የተነሳ ተካልቦ ሲያካልበኝ፣ ሮጦ ሲያስሮጠኝ፤ ምናልባት የዚያ የሞተው ሰውየ ዘመድ ሆኖ ተቤቱ ስደርስ ቢበቀለኝስ ብየ ማሰቤና መጨነቄም አልቀረም፡

‹‹ የእኔ እማዬ ይሄ ዓይነቱ ክፉ አሳብ ከራሴ ላይ የሚያገፈው፤ ሥጋውን ያሸከመኝ ሰውየ ከቤቱ እንደደረስን፣ የኔን ሚጢጢ ረስቶ ያንን የገዛውን ሥጋ ከጠረጴዛ ላይ አጋድሞ፤ ‹ ቶሎ በይ! ... ቢላ አምጪ ... › እያለ በሚስቱ ላይ የትእዛዝ ናዳ ሲያወርድና፤ አስሬ ምራቁን እየዋጠ እጆቹን ሲያፋትግ ሳይ ነው፡ ይሄኔ ቀስ ብየ ዘንቢሌን አንጠልጥየ እሾልክና ወደ ሉካንዳ ቤቱ እፈረጥጣለሁ፡ ግና ምን ያደርጋል! ምን ያህል ራሴን ሰውሬ ስርቻ ለስርቻ እየተሸለኮለኩ ብጓዝም፤ ወሬኛው ሁላ ሲያየኝ ‹ ያውና

ያ ሰዉዬዉን የገደለዉ ልጅ! … › እያለ ማገድ አላስኬድ ይለኛል፡፡ ይሄኔ ያዉ እንደተለመደዉ የሆድ ብሶቴን በእምባየ እበሳ እየተዉጥሁ፤ ግራና ቀኝ ሳልገላመጥ ወደ ሉካንዳ ቤቱ እሸመጥጣለሁ።

‹‹ እማዬ አንቺ አይደለሽ ‹ ሰዉ መርዳት ጥሩ ነዉ፤ የደከመ ማገዝ ያስፈልጋል፣ ከመርዳት ምርቃት ይገኛል › ብለሽ የምትመክሪኝ? እማዬ ሰዉ መርዳቴ ግን ለኔ እርግማን ነዉ የሆነብኝ፡፡ ጉድሽን አላወቅሽም ለካ! ሰዉየዉ እንደሞተ እስር ቤትም ልገባልሽ ነበር እኮ! ይህ እጀ ቆራጣ ደንበኛዉ ጋሼ ቶልቻ ጋ መጥቶ ጥሬ ስጋ አስቆረጠና ተቀመጠ፡ ‹ ሂደና እየቆረጥክ አጉርሰዉ › አለኝ ጋሼ ቶልቻ፡ ረዳሁት፡፡ ሰዉዬዉ ሥጋዉን አላኘከዉ ኖሮ ከጉሮሮዉ ተዉተፈ፡፡ ዐይኔ እያየዉ ተንፈራፍሮ ሞተ፡፡ እማዬ እኔ ልገድለዉ አላጎረስኩትም፡ ሰዉ ግን ዐይንህን ለአፈር አለኝ፡፡ ፖሊስ ወደ ቤትህ ሂድ አለኝ እንጂ እዚያዉ አስረዉኝ ባቆዩኝ ኖሮ እላለሁ። የሰዉ ዐይን ሞት ፈራሁ።

‹‹ሰዉዬዉ ታንቆ እንደሞተ የተፈጠረዉን ግርግርና የደረሰብኝን እንግልት ብታይ እማዬ ሐዘኑን አትችይዉም ነበር፡፡ እንኳንም በአጠገቤ አልኖርሽ፡፡ ሰዎች ጩሁሽ የኔ ያልሆነ ታሪክ ፈጥረዉልኝ መድረሻ እስኪጠፉኝ አሸማቀቁኝ፣ ዘቱብኝ፡፡

‹‹ሰዉ ከቦኝ እንደዚያ ልዩ አዉሬ አርጎኝ ሲራገም ብታይ እማዬ፣ ሰዉየዉ ስለሞተዉ ሰዉዬ ሳይሆን ስለኔ ብለሽ ልብሽ በሀዘን ይሰበር ነበር፡፡ እንዲያዉ ምን ብለዉት ይሆን እንዲህ ልጄ የተማረረዉ ብለሽ እንዳታሰላስይ የማታዉቂዉን ጥቂቱን ላካፍልሽ፡፡ አንቺን ለማስሰብ ብዬ ሳይሆን እንዲያዉ የደረሰብኝን የልብ ስብራት የማካፍለዉ ሰዉ ስላጣሁ ነዉ።

‹‹ይሄዉልሽ አደጋዉ የደረሰ እለት አንድ ግብዳ የሚያህል መዳፍ ማጅራቴን ጨምድዶ እንደያዘኝ ልብ አላልኩም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሰማይ ምድሩ ዞሮብኛል፡፡ የሟቹን ሰዉዬ አስከሬን አምቡላንስ ወደ ፍቼ ጤና ጣቢያ ሲወስደዉ፤ እኔን ጨምድዶ የያዘኝ መዳፍ ደሞ እያዳፋ ከቀበሌ አደረሰኝ፡፡ ቀበሌም ተቀብሎ ለፖሊስ ጣቢያ አሳለፈኝ፡፡

እኔ ከፖሊስ ጣቢያው ደጃፍ ቆሜ ፍርሀት ሰቅዞ እያርገፈገፈኝ ነው፡ አላፊ አግዳሚው በዓይንና በአፉ አመናጨኝ፡፡ ሙዳ ምኑን የማያሰላብኝ፣ የማይተቸኝ፣ የማይረግመኝና የማይሰድበኝ የሰው ዓይነት አልነበረም፡ ምን ያልተባልኩት ነገር አለ?

‹‹አንድ ፍሬ ልጅ እኮ ነው! ... ምን ዓይነቱ ጨካኝ ቢሆን ነው አበ? !...›› ይለኛል አንዱ

‹‹ጨካኝ ብቻ ትላለህ እንዴ?... አረዩስ የሰይጣን ቁራጭ እንጂ!...›› ይላል ሌላው

‹‹ይሄ አውሬ ነው እንጂ፣ ከሰው ዘር የተፈጠረም አይደል ... አሲዳም!...›› ይቀበላል ሌላው ተራጋሚ

‹‹እቆራጣ እጁ ላይ በተንዘለዘለው እጅጌው ነው አሉ – አንቆ የገደለው...›› ይላል ደሞ ሌላው፡

‹‹የለም የለም!... በካራ ወግቶ ነው። ይሄ ሽንፍላ ገልባጭ ጥጋበኛ!...›› ይመልሳል ሌላኛው

‹‹ይሆናል! ይሆናል!... ወግቶ ነው። አንገት ላንገት ተናንቆስ ትልቁን ሰውዬ ሊገለው አይችልም! ››

‹‹ጥጋበኛ ብጤ ነው ያስታውቃል!... ዓይኖቹን ደም አስለብሶ ሲያጉረጠርጥ አታየውም?...››

እንዲህ እንዲህ እያሉ ነው የተቀባበሉኝ፡፡ እኔ ግን ተግራና ተቀኝ የሚነዘርብኝን ትችትና እርግማን በሰማሁ ቁጥር ይብልጥ ጨነቀኝ፡፡ ከመደንገጤም የተነሳ ያ አንቺ የምታደንቂው ጠይሙ የገፄ ቀለም ተለውጦ አመድ የተነፋበት ቁርበት መምሰሉ ይሰማኝ ነበር፡፡ ከሰውነቴም ላይ ሙዳ ሙዳ ሥጋ የተነሳለት ነበር የሚመስለኝ፡፡

(ምንጭ የነገ ናፍቆት ፡ ገፅ 80 – 83)

***ትዕዛዝ – ከላይ በቀረበው ምንባብ አንብባችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡***

1. ባለታሪኩ የሆዱን ብሶት ሲገልፅበት የነበረው ማገድ በምንድን ነበር?

2. ባለታሪኩ ሰው ገደለሀል የተባለው በምን ምክንያት ነው?

3. ባለታሪኩ ሰው ገደለሀል ተብሎ መጀመሪያ የተወሰደው የት ነው?

4. ተግሪና ተቀኝ **የማቢነ ዘርብሽን** ትችትና እርግማን በሰሙሁ ቁጥር ይብልጥ ጨቀኝ፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው?

5. አላፊ አግዳሚው በዓይንና በአፉ **አማኝ**፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው?

6. በምንባቡ ውስጥ በይበልጥ ጎልቶ የሚታየው የዘይቤ ዓይነት የትኛው ነው? ምሳሌ በማቅረብ ግለፁ?

7. ባለታሪኩ እናቱን እንኳንም በአጠገቤ አልኖርሽ፡፡ ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

8. ባለታሪኩን ሰውን መርዳት ርግማን ሆነብኝ ያለው በምን ምክንያት ነው?

9. ምንባቡን በአንድ አንቀፅ አሳጥራችሁ ፃፉ?

10. የምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት ምንድን ነው?

**አባሪ 3.**

**ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ**

**ውድ መምህር ከዚህ በታች ለቀረበት ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው ስለተገኙ ከልብ እያመሰገንኩ ከዚህ በታች የቀረበትን ጥያቄዎች ከመፃፍ ማስተማሩ ሂደት አንፃር የሚሰማዎትን መልስ ይስጡ፡፡**

1. የንባብ ክሂልን ሲያስተምሩ አዘውትረው የሚጠቀሙት የትኛውን የንባብ ሂደት ነው? ለምን?
2. በንባብ ክሂል ትምህርት ጊዜ ለማስተማር ቀላል ነው ብለው የሚያስቡት ሂደት የትኛው ነው?
3. በመፃፍ ማስተማሩ ሂደት የማንበብ ክሂልን ሲያስተምሩ የተማሪዎች የማንበብ ብልሀት ምን ይመስላል?
4. የተማሪዎች የንባብ ፍላጎት (የማንበብ ብልሀት) የመፃፍ ፍላጎት በመምህሩ ጥረትና አቀራረብ ይወሰናል ብለው ያምናሉ?

**ማረጋገጫ**

ይህ የጥናት ፅሁፍ የእኔ መሆኑን ለጥናቱ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናት ዋቢነታቸው በትክክ የተጠቀሱ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡

ስም ______________________________

ፊርማ______________________________

በታ አማርኛ ትምህርት ክፍል ትምህርት ፋካልቲ ጅማ ዩኒቨርስቲ

ቀን______________________________

በአማካሪነቴ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ስራው በማጠናቀቁ ለፈተና እንዲቀርብ መስማማቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ______________________________

ፊርማ______________________________

ቀን________________________________